https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ የካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year, No.14
ADDIS ABABA 17th February, 2020

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፬/፪ሺ፲፪ ዓ.ም
የፌደራል ማረሚያ ቤት አዋጅ.....ገጽ ፲፪፻ሺ፩፻፪

Content

Proclamation No. 1174/2019
Federal Prison Proclamation……Page 12102

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፬/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የፌደራል ማረሚያ ቤት አዋጅ

የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥትንና ሕገ መንግሥቱን መሠረት አድርገው የወጡ ሕጎችን፣ ሐገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የእስረኛ አያያዝ ደረጃዎችን ባከበረ ሁኔታ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን ማስፈፀም በሚያስችል ሁኔታ ማደራጀት በማስፈለጉ፤

ማረሚያ ቤቶች የእስረኞችን ሰብአዊ ክብርና መብት በማክበር እንዲሁም የእስረኞቹ ግላዊ ሁኔታ በሚጠይቀው የፍርድ አፈፃፀምና እርማት ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግና ከሕብረተሰቡ ጋር የሚቀላቀሉበትን ሥርዓት መደንገግ በማስፈለጉ፤

እስረኞች ባላቸው የአደገኛነት ባህሪ ወይም ባላቸው የጉዳት ተጋላጭነት ወይም በፆታቸው እንዲሁም ከፍርድ በፊት በማረፊያ ቤቶች የሚቆዩ እስረኞች ሊደረግላቸው የሚገባውን አያያዝ መደንገግ በማስፈለጉ፤

ማረሚያ ቤቶች ለእስረኞች እንዲሁም ለመላው ሕብረተሰብ በእኩልነትና በፍትሐዊነት የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ሕጋዊ ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

PROCLAMATION No. 1174/2019

FEDERAL PRISON PROCLAMATION

WHERE AS, it is found necessary to establish the Federal Prison Commission in a manner that would allow it enforce court decisions that respect the FDRE Constitution and laws enacted pursuant to it, international agreements Ethiopia is a party to or has ratified, and internationally recognized standards for the treatment of prisoners;

WHERE AS,it is necessary to put in place a system whereby prisoners are reintegrated into society, prisons respect the human dignity of prisoners and enforce judicial orders and corrective measures based on the particular circumstances of the prisoners;

WHERE AS, it is found necessary to provide for provisions on treatment of prisoners and those in custody on remand based on the degree of danger they pose and their level of vulnerability including on account of gender;

WHERE AS, putting in place an efficient legal framework where prisons treat prisoners as well as society based on principles of equality and fairness is found necessary;

https://chilot.me

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌደራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፬/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ "ኮሚሽን" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመው የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ነው፤

፪/ "የማህበረሰብ መሪዎች ኮሚቴ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ መሠረት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

፫/ "የማረሚያ ፖሊስ" ማለት መሠረታዊ የሆነ የማረሚያ ፖሊስ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ተቀጥሮ የሚሠራ የማረሚያ ቤት ፖሊስ ነው፤

፬/"የጋራ ጉባኤ" ማለት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀኔራል፣ ምክትል ኮሚሽነር ጀኔራሎች እና የክልል ማረሚያ ቤት ኃላፊዎችን የሚያካትት ጉባኤ ነው፤

፭/ "ማረሚያ ቤት" ማለት ለሕዝብ በግልጽ የሚታወቅ ታራሚዎች የተወሰነባቸውን ፍርድ የሚፈፅሙበ፣ የሚታረሙበትና የሚታነፁበትን እንዲሁም ማረፊያ ቤትን ይጨምራል፤

፮/ "ማረፊያ ቤት" ማለት የመደበኛ ክስ ተከፍቶ በቀጠሮ ላይ ያሉ ተከሳሾች ወይም በፍትሐ ብሔር የአፈፃፀም ክርክር በተሰጠ ትዕዛዝ የሚቆዩበት ነው፤

፯/ "እስረኛ" ማለት ታራሚ፣ተከሳሽ ወይም የፍትሐብሔር ታሳሪ ነው፤

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Federal Prison Proclamation No.1174/2019.

2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "Commission" means the Federal Prison Commission established by this Proclamation;

2/ "Community Leaders Committee" means Committee established pursuant to Article 13 of this Proclamation;

3/ "Prison Police" means police who is employed by the Federal Prison Commission after undergoing a basic training in prison warden ship.

4/ "Joint Council" means the joint council that includes the Commissioner General, Deputy Commissioner Generals of the Commission and officials of regional prisons.

5/ "Prison" means a publicly known Federal Correctional Institution where sentenced prisoners serve their terms, are reformed and rehabilitated; and includes custodial places for prisoners held on remand.

6/ "Detention Center" means place where arrested persons held on remand are kept or place where judgment debtors in civil proceedings are held.

7/ "convicted prisoner" means prisoner under correction, accused person or detainee of civil proceedings.

https://chilot.me

፰/ "ታራሚ" ማለት በፍርድ ቤት የተወሰነበትን ፍርድ በማረሚያ ቤት ውስጥ በመፈፀም ላይ የሚገኝ ሰው ነው፤

፱/ "ተከሳሽ" ማለት በወንጀል ፍርድ ሂደት ማረፊያ ቤት የሚቆይ ሰው ነው፤

፲/ "የፍትሐ ብሔር ታሳሪ" ማለት በፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር የአፈጻጸም ክርክር በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ሰው ነው፤

፲፩/ "ወጣት እስረኛ" ማለት እድሜው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆነ እና ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ እስረኛ ነው፤

፲፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤

፲፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬/ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል።

፫.መርህ

፩/ የማረሚያ ቤት አያያዝ የእስረኞችን ሰብአዊ ክብር እና መብታቸውን በማክበር ታርመው እና ታንፀው ሕግ አክባሪ፣ መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው፣ ሠላማዊና አምራች ዜጎች ሆነው ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ የሚያስችል ይሆናል።

፪/ ኮሚሽኑ የሙያ እና የአሰራር ነጻነት ይኖረዋል።

፫/ ኮሚሽኑ ለሕግ፤ ለመንግሥት እና ለሕዝብ ያለበትን ተጠያቂነት በማረጋገጥ ሥራውን በግልፀኝነት ያከናውናል።

፬/ ኮሚሽኑ ከአድሎ የፀዳና የሁሉንም እስረኛ መብት በእኩል የሚያከብር አሰራር ይኖረዋል።

፭/ ሕግ አክባሪ፣ በሥነ-ምግባር እና ሙያ ብቃት የታነፀ፣ ከሙስና የፀዳ እና የህዝብ አገልጋይ የማረሚያ ቤቶች ሥርዓት ይዘረጋል።

8/ "Prisoner " means a convicted prisoner serving a sentence term.

9/ "Accused Person" means a person held in custody on remand in a criminal proceeding.

10/"detainee of civil proceeding" means a person detained upon judicial order in a civil proceeding.

11/"Juvenile prisoner" means a prisoner between the age of fifteen and eighteen.

12/''Regional State'' means any state referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

13/"Person "means a natural or legal person;

14/Expressions in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

3. Principle

1/ Treatment of prisoners shall ensure prisoners are treated with human dignity they deserve, and that they are reformed to be law abiding citizens with good conduct and become peaceful and productive members of the community they reintegrate into.

2/ The Commission shall have professional as well as operational autonomy.

3/ The Commission shall, ensuring its accountability to the law, government and the people, carry out its obligations in a transparent manner.

4/ The Commission shall have operational rules and practices that are impartial and respect the rights of every prisoner equally.

5/ The Commission shall put in place a prison administration system that ensures respect for the law, is ethical and professionally competent, incorruptible and is at the service of society.

https://chilot.me

ክፍል ሁለት

የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን

፬. መቋቋም

፩/ የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን") እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

፪/ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ ይሆናል።

፭. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም የሀገሪቱ ክልል ወይም ቦታ ቅርንጫፍ ሊያቋቁም ይችላል።

፮.የኮሚሽኑ ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ የፍርድ ቤት ትዕዛዝና የቅጣት ውሳኔ በማስፈፀም፣እስረኞችን በመቀበል፣ መብታቸውን በማክበር፣ ሰብአዊ ክብራቸውን በመጠበቅና መሠረታዊ ፍላጎታቸውን በማሟላት፣ ለእስረኞች የሥነ-ልቦና፣የቀለምና የሙያ ሥልጠና በመስጠት የአስተሳሰብና የሥነ–ምግባር ለውጥ እንዲያመጡና ሕግ አክባሪ፣ ሠላማዊና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

፯. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ለሕገ-መንግሥቱ እና ለሙያው ታማኝ የሆነ፤ ዕውቀትና ክህሎት ያለው የማረሚያ ፖሊስ እና የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ለማፍራት የራሱ የሆነ የማሰልጠኛ ተቋም ያቋቁማል፣

፪/ የማረሚያ ቤት የፖሊስ አባላት በውጭ ሀገር የትምህርትና ስልጠና ዕድል እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፫/ በደንብ መሰረት ለማረሚያ ፖሊስ የማዕረግ

PART TWO

FEDERAL PRISON COMMISSION

4. Establishment

1/ A Federal Prison Commission (hereinafter called the "Commission") is hereby re-established as an autonomous Federal Government Organ having its own legal personality.

2/ The Commission shall be accountable to the Federal Attorney General.

5. Head Office

The head office of the Commission shall be in Addis Ababa and may have branch offices in any region or any part of the country where necessary.

6. Objective of the Commission

The objectives of the Commission shall be enforcing sentences and judicial orders, respecting the rights of prisoners under its care, fulfilling their needs and upholding their human dignity; offer psychological, academic and vocational trainings to prisoners so that they are ethically as well as attitudinally rehabilitated which will in turn help in ensuring that they are law abiding, peaceful and productive citizens.

7. Powers and Duties of the Commission

The Commission shall have the following powers and duties.

1/ establish its own training institution to produce prison police and social science professionals loyal to the Constitution and their profession and have the required knowledge and skills.

2/ facilitate abroad opportunities for prison police trainings and education;

3/ put into effect a system of promotion and appointment of prison police members to a higher rank, pay raise,

https://chilot.me

ሹመት፣ የዕርከን ጭማሪ፣ የኃላፊነት ክፍያና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

position allowances and other benefits pursuant to a Regulation.

፬/ ለማረሚያ ፖሊስ የጋራ መኖሪያ ካምፖችን ይሠራል፤

4/ build prison police residential camps.

፭/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት የሚላኩለትን እስረኞች ይቀበላል፤ ይጠብቃል፤ ያስተዳድራል፤ ያጅባል፤ ፍርድ ቤት ያቀርባል፤ ያርማል፤ ሌሎች በሕግ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞችን ይፈፅማል፤

5/ receive, protect, manage, escort, produce in courts of law, reform prisoners sent to it by court decisions or order; shall also execute other orders of courts having competence.

፮/ ለእስረኞች ምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳትና ነፃ ሕክምና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

6/ provide food, shelter, clothing and free medication for prisoners.

፯/ ለእስረኞች ግንባታና ምርታማነት የሚያግዙ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ያደራጃል፤

7/ set up educational and training facilities with a view to enhancing the productivity and personal development of prisoners.

፰/ታራሚዎችን በተመቻቸ ቦታ ማረምና ማነፅ የሚያስችሉ አዳዲስ የማረሚያ ቤት ማዕከላትን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ገንብቶ ያስተዳድራል፤

8/ build and administer new prison facilities across the country to rehabilitate prisoners adequately.

፱/ ታራሚዎችን ለማረም፣ ለማነፅ እና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ያደራጃል፤ ይሠራል፤

9/ Work towards the correction,development, and productivity of prisoners.

፲/ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በሚያገኙት ትምህርትና ሥልጠና በቂ የንድፈ ሐሳብ እውቀትና ክህሎት አዳብረው የሥራ ባህልና አምራች ዜጋ ሆነው እንዲወጡ የሚያስችሉ ኢንዱስትሪዎችን ያቋቁማል፤

10/ establish industries that could realize the theoretical knowledge and skills prisoners possess in becoming productive work force.

፲፩/ ታራሚዎች በሕጉ መሠረት በአመክሮ ወይም በይቅርታ ለመፍታት የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው ሲገኙ በሚወጣው ደንብ፣ መመሪያና በተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት በአመክሮ ወይም በይቅርታ እንዲፈቱ ለይቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ውሳኔ ሲያገኝም ተግባራዊ ያደርጋል፤

11/ submit lists of prisoners to be released by parole or pardon those who meet preconditions to be released by parole or pardon according to a Regulation and Order to be enacted and according to the established procedures and release them upon a decision to that effect.

፲፪/ ለማረሚያ ቤት አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ

12/ make prison resources and facilities such as prison

https://chilot.me

ትጥቅ፣ ተሽከርካሪ፣ የሬዲዮ መገናኛ፣ የፍተሻና የአድማ ብተና መሣሪያዎች፣ ሲሲቲቪ ካሜራና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

security equipment, vehicle, radio communication equipment, search and riot control equipment, CCTV cameras and other such technological devices and equipment available.

፲፫/ በሐገር አቀፍ ደረጃ የማረሚያ ቤቶችን አገልግሎት ለማሻሻል የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችን ያደርጋል፤

13/ undertake studies and research with a view to improving prison conditions nationally.

፲፬/ በሐገር አቀፍ ደረጃ የእስረኞች መረጃዎችን እና ስታትስቲክሶችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፤

14/ collect, analyze and interpret data and statistics of prisoners nationally.

፲፭/ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ከማረሚያ ቤቶች የሚገኙ የልማትና ሌሎች የውስጥ ገቢዎችን፤ ለእስረኞች ማኅበራዊ አገልግሎት ማሻሻያ እና ለአቅም ግንባታ ሥራዎች እንዲውል ያደርጋል፤

15/ deploy resources generated through various income generating schemes within the prison system,, according to relevant laws, to improve the social conditions of prisoners and capacity building initiatives.

፲፮/ በአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ አዋጁ መሠረት የትራንስፖርት ባለሥልጣን የሚዘረጋውን ሥርዓት ጠብቆ ለፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የውክልና ፈቃድ ሲሰጠው ለታራሚዎችና ለማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት ተሽከርካሪ መንዳት የሚያስችል ሥልጠና በመስጠት ከትራንስፖርት ባለስልጣን የአሽከሪካሪነት የብቃት ማረጋገጫ ተፈትነው እንዲወስዱ ያደርጋል።ዝርዝሩ በደንብ ይወሳናል፤

16/ With due consideration for the procedures laid by Transport Authority Qualification Certificate Proclamation, the Commission upon the authentication by the Authority offer driving training to prisoners and its personnel through competency certificate issued by Transport Authority.The details shall be determined by a Regulation .

፲፯/ ሥልጣንና ተግባሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

17/ Communicate with relevant government and non-governmental organizations in matters relating to its powers and duties;

፲፰/የክልልና የፌደራል ማረሚያ ቤቶች የጋራ ጉባዔ በጋራ ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣

18/ jointly establish a Joint Council of Regional and Federal Prison and coordinate it.

፲፱/ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚሰጠው ቅድሚያ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ማረሚያ ቤቶች የአቅም ግንባታ፣ የሙያ እገዛ እና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

19/ Without prejudice to the priority given to regions seeking special support, offer capacity building support, professional assistance and advisory support to regional prison .

፳/ በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት

20/ put in place alternative correctional measures up on

https://chilot.me

ታራሚዎችን ለማረም የሚረዱ አማራጭ የእርምት መንገዶችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፩/እርምት ጨርሰዉ ወይም በሌሎች ምክንያት ከእስር የወጡ ታራሚዎችን ከሌሎች ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ከእስር ሲወጡ በተቀመጠላቸዉ የጠባይ አመራር መሰረት ስለመፈጸማቸዉ ክትትል ያደርጋል።

፳፪/ውል ይዋዋላል፤ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ በራሱ ሥም ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

፳፫/ተልኮውን መሠረት በማድረግ ሕግ ያስከብራል፤

፳፬/ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፰. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነር ጄኔራል እና ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራሎች፣

፪/ የማረሚያ ፖሊስ አባላት እና ሲቪል ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

፱. <u>የኮሚሽነር ጄኔራሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ኮሚሽነር ጄኔራሉ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነር ጄኔራሉ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፯ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኮሚሽነሮች፣ የምክትል ኮሚሽነሮችንና የረዳት ኮሚሽነሮችን የማዕረግ ሹመት እንዲፀድቅ ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ያቀርባል፤ ከዚህ ውጭ ያሉ የማዕረግ ሹመት ይሰጣል፤በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት የሥራ ምደባ ያከናውናል፤ ያሰናብታል፤

decision of court.

21/ supervise in cooperation with other concerned bodies whether prisoners released from jail having served their sentences or those released for different reasons have complied with behavioral management plan set during their release.

22/ enter into agreements, own property, sue and be sued in its own name.

23/ enforce the law based on its mission.

24/ carry out other activities that could help execute its objectives.

8. <u>Organization of the Commission</u>

The Commission shall have:

1/ a Commissioner General and Deputy Commissioner Generals to be appointed by government; and

2/ Prison police officers and civil personnel.

9. <u>Powers and Duties of the Commissioner General</u>

1/ The Commissioner General shall be the chief executive officer of the Commission, direct and manage the duties and responsibilities of the Commission;

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the Commissioner General shall:

a) enforce powers and duties of the Commission provided for under Article 7 of this Proclamation.

b) submit the nomination for promotion of Commissioners, Deputy Commissioners and Assistant Commissioners for approval by the Attorney General; promote and assign other ranks,employ and dismiss same according to Regulation or Directive to be issued.

https://chilot.me

ሐ) ከሕዝብ፣ ከእስረኞች፣ ከኮሚሽኑ አባላትና ሠራተኞች የሚቀርቡለትን ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ይቀበላል፤ እንዲጣራ ያደርጋል ፤ ይወስናል፤

መ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የማረሚያ ፖሊስ አባላትን፤ ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል ፤ ያሰናብታል፤

ሠ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ድጋፍ ሰጪ የሲቪል ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል ፣ ያሰናብታል፤

ረ) ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና ሪፖርትን በማዘጋጀት ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ያቀርባል፤

ሰ) ለኮሚሽኑ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድ በሥራ ፕሮግራሙ መሠረት ገንዘብ ወጪ ይፈቅዳል፤

ሸ) የውስጥ አዲት ሥራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል፤ የሒሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፤

ቀ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል።

፫/ ኮሚሽነር ጄኔራሉ ለሥራው ውጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል በኮሚሽኑ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፲. <u>የምክትል ኮሚሽነር ጄኔራሎች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራሎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

፩/ በዘርፍ የሚሰተጣቸውን መደበኛ ሥራዎች ያከናውናሉ፤

፪/ የኮሚሽኑን ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነር ጄኔራሉን ይረዳሉ፤

፫/ በኮሚሽነር ጄኔራሉ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናሉ፤

c) receive, inquire into and decide on complaints and grievances directed to it from the public, prisoners, members of the Commission and its personnel;

d) recruit, employ, administer and dismiss prison police according to regulation to be issued by the Council of Ministers.

e) employ, administer and dismiss supporting staff of the Commission according to Federal Civil Service laws

f) submit yearly work plan, work programs and report to the Federal Attorney General;

g) prepare a yearly budget for the Commission and authorize expenditure where the work plan and the budget proposal is approved.

h) Cause the conduct of internal auditing; submit financial report.

i) represent the Commission in its dealings with third parties.

3/ The Commissioner General may delegate part of his responsibilities and duties to the other officials of the Commission to the extent necessary for the successful implementation of its duties.

10. <u>Powers and Duties of the Deputy Commissioner General</u>

Deputy Commissioner General shall:

1/ carry out regular duties of divisions to which they are assigned;

2/ assist the Commissioner General in the planning, organization, direction and coordination of the Commission's responsibilities;

3/ carry out such other duties as are specified by the Commissioner General; and

https://chilot.me

፬/ ኮሚሽነር ጄኔራሉ በማይኖርበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ ካልወከለ በስተቀር በማዕረግ ሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራል ኮሚሽነር ጄነራሉን ተክቶ ይሠራል።

4/ Represent the Commissioner General, in the absence of the Commissioner General, unless the senior deputy Commissioner General is delegated under special circumstances.

፲፩.በጀት

ኮሚሽኑ በፌደራል መንግሥት ከሚመመደብለት በጀት በተጨማሪ ከውስጥ የሚያገኘውን ገቢ የገንዘብ ሚኒስቴርን እያስፈቀደ ሊጠቀም ይችላል።

11.Budget

In addition to the allocated budget from the Federal Government, the Commission may utilize its internal revenue through permission of the Ministry of Finance.

፲፪. የሂሣብ መዛግብትና ምርመራ

፩/ ኮሚሽኑ የተሟላ እና ትክክለኛ የሆኑ የሒሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኮሚሽኑ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

12. Auditing and Books of Accounts

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts of the Commission or financial documents shall be audited yearly by the Auditor General or an auditor designated by it.

ክፍል ሦስት
የማህበረሰብ መሪዎች ኮሚቴ

PART THREE
COMMITTEE OF COMMUNITY LEADERS

፲፫. የኮሚቴው መቋቋም

፩/ የእስረኞችን አያያዝ የሚከታተልና የሚቆጣጠር የበጎ ፈቃደኞች የማህበረሰብ መሪዎች ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ ኮሚቴ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

13. Establishment of the Committee

1/ The voluntary Community Leaders Committee (hereinafter called ''the Committee'') that supervises and monitors the treatment of prisoners is hereby established.

፪/ የበጎ ፈቃደኞች የማህበረሰብ መሪዎች ኮሚቴ አባላት በህብረተሰቡ የታወቁና ተቀባይነት ያላቸዉ የማህበረሰብ መሪዎች በተለይ የሃይማኖት መሪዎች፣ የባህላዊ ስርዓት መሪዎች ፣የአገር ሽማግሌዎች ፣የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና የመሳሰሉት ሆነው ያታዊ ስብጥርን መሠረት ያደረገ ይሆናል፤

2/ With due consideration of gender disparity, members of the Community Committee shall be well known individuals recognized in the community, especially religious leaders,cultural leaders, elders, human right advocates, famous individuals and the like.

፫/ ቁጥራቸው በመንግሰት የሚወሰን የኮሚቴ አባላት ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ በጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ አቅራቢነት በመንግስት ይሾማሉ።

3/The Members of the Committee, including the Chairperson, shall be appointed by the Government upon recommendations of the Attorney General; and their number small be determined by the Government.

፬/ የኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አምስት አመት

4/The term office of Committee members shall be

https://chilot.me

ይሆናል። ሆኖም ድጋሚ ለተጨማሪ አምስት አመት ሊሾሙ ይችላሉ።

፭/ የኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላይ ዓቃቢ ሕጉ ይሆናል።

five years. But any member may be appointed for another five years.

5/The Committee shall be accountable to the Attorney General.

፲፬. <u>የኮሚቴው ስልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው ፡-

14. <u>Powers and Duties of the Committee</u>

The Committee shall፡ -

፩/ የማረሚያ ቤት ኮሚሽን ለእስረኞች የሚያደርውን አያያዝ ህገ መንግስቱን፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ፣ ይህን አዋጅ እና ሌሎች ህጎችን ያከበረ መሆኑን ያረጋግጣል።

1/ ensure the treatment of prisoners by the Commission respects the Constitution, international human rights agreements Ethiopia has accepted, this Proclamation and other relevant laws.

፪/ የእስረኞች አያያዝን ለማሻሻል ከባለድርሻ አካላት ጋር በምክክር ይሰራል።

2/ consult with the relevant stakeholders on the improvement of the treatment of prisoners.

፫/ የእስረኞች አያያዝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተውን ያላከበረ በሆነ ጊዜ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ሪፖርት ያደርጋል።

3/ Where the treatment of prisoners did not comply with provisions indicated under sub-article (1) of this Article, submit a report to the Attorney General for corrective measures.

፲፭. <u>የኮሚቴው ጽሕፈት ቤት</u>

ኮሚቴው በጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ የሚደራጅ የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል።

15. <u>Secretariat of the Committee</u>

The Committee shall have its own secretariat to be organized by the Attorney General.

፲፮. <u>የኮሚቴው ስብሰባና ውሳኔ</u>

16. <u>Committee Meetings and Decisions</u>

፩/ ኮሚቴው ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

1/ The Committee shall hold meeting at least once in three months. But when necessary it can meet at any time up on notice of the chairperson.

፪/ ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሚላል።

2/ A quorum shall be constituted where more than half of the Committee members are in attendance.

፫/ የኮሚቴው ውሳኔዎቹን በተገኙ አባላት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ይወስናል።

3/ The Committee shall give its decisions by a two-thirds majority of those in attendance.

፬/ ኮሚቴው የራሱ የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

4/ The Committee may issue its own rules of procedure.

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የማረሚያ ፖሊስ አስተዳደር</u>

<u>PART FOUR</u>

<u>PRISON POLICE ADMINISTRATION</u>

https://chilot.me

፲፮. <u>የአገልግሎት ዘመን</u>

የማረሚያ ፖሊስ የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

፲፯. <u>የማረሚያ ፖሊስ መብት</u>

የማረሚያ ፖሊስ:-

፩/ በፌደራል መንግሥት በሚፀድቅ የደሞዝ ስኬል መሠረት ደመወዝ ያገኛል፤

፪/ በኮሚሽኑ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቀለብ፣ ልዩ ልዩ አበሎች፣ የደንብ ልብስና የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

፫/ ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በኮሚሽኑ ወጪ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል።ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

፬/ ከሥራው ጋር በተያያዘ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሥራት ችሎታውን በዘላቂነት ሲያጣ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል፤

፭/ የሥልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፲፰. <u>የማረሚያ ፖሊስ ግዴታ</u>

የማረሚያ ፖሊስ:-

፩/በሕገ-መንግሥቱና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች የተረጋገጡ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሙሉ በሙሉ በማክበር እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ሥራውን የማከናወን፣

፪/ ኮሚሽኑ በሚያስቀምጠው አሠራርና አደረጃጀት መሠረት ሥራውን የመስራት፤ በቡድን ሥራዎች እና ውሳኔዎች የጋራና የነጠላ ኃላፊነት መውሰድ።

፲፱. <u>ቃለ መሐላ</u>

ለማረሚያ ፖሊስ ሥራ የተቀጠረ ምልምል

17. <u>Term of Service</u>

The compulsory term of service of a prison police shall be seven years. Particulars shall be determined by Regulation.

18. <u>Rights of Prison Police</u>

A prison police officer shall be entitled to:

1/ a salary according to the scale approved by the Federal Government;

2/ ration, allowances, uniform and medical services in accordance with the administrative regulation of the Commission;

3/ the services of an attorney at law at the Commission's expense for liabilities incurred while carrying out his task within the scope of his duties. Particulars shall be determined by regulation

4/ pension in accordance with the pertinent law when he permanently loses his working capacity fully or partially because of an accident in connection with his duties; and

5/ lodge complaints by following existing hierarchy.

19. <u>Obligations of Prison Police</u>

A prison police officer shall discharge his duties:

1/ by fully respecting the fundamental rights and freedoms enshrined in the Constitution and treaties ratified by Ethiopia as well as in accordance with other relevant laws; and

2/ in accordance with the operational rules and institutional setup put in place by the Commission. And shall entail joint and several responsibilities of group operations and decisions.

20. <u>Oath</u>

Every recruit employed as a prison police shall take oath

https://chilot.me

ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ሙያዊ ኃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሐላ ይፈጽማል። የቃለ መሐላው ይዘት በደንብ ይወሰናል።

፳፩. <u>ስለማዕረግና ምልክት</u>

፩/ ኮሚሽኑ የተለያዩ ደረጃዎች ያላቸው የማረሚያ ፖሊስ ማዕረግና ምልክት ይኖረዋል።

፪/ የማረሚያ ፖሊስ ደረጃውንና ኃላፊነቱን የሚገልጽ የማረሚያ ፖሊስ ማዕረግና ምልክት ይኖረዋል።

፳፪. <u>የማረሚያ ፖሊስ ማዕረግና የሥልጣን ደረጃ</u>

፩/ የማረሚያ ፖሊስ ማዕረጎች የሚከተሉት ይሆናሉ:-

ሀ) ኮንስታብል፤

ለ) ረዳት ሳጅን፤

ሐ) ምክትል ሳጅን፤

መ) ሳጅን፤

ሠ) ዋና ሳጅን፤

ረ) ረዳት ኢንስፔክተር፤

ሰ) ምክትል ኢንስፔክተር፤

ሸ) ኢንስፔክተር፤

ቀ) ዋና ኢንስፔክተር፤

በ) ምክትል ኮማንደር፤

ተ) ኮማንደር፤

ቸ) ረዳት ኮሚሽነር፤

ኀ) ምክትል ኮሚሽነር፤

ነ) ኮሚሽነር፤

ኘ) ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራል፤እና

አ) ኮሚሽነር ጄኔራል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተመለከቱት የሥልጣን ደረጃዎች ውስጥ በፊደል (ኘ) እና (አ) በስተቀር ሌሎች የማረሚያ ፖሊስ ማዕረጎች የየራሳቸው ምልክት ይኖራቸዋል።

፳፫. <u>ሜዳይ፣ ሪባን፣የምስክር ወረቀት፣ ሌሎች ሽልማቶች</u>

of loyalty to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia in carrying out the public responsibility and professional responsibility entrusted to him. The contents of the oath shall be determined by Regulation.

21. <u>Ranks and Insignia</u>

1/ The Commission shall have different levels of prison police ranks and insignia.

2/ A prison police officer shall have prison office rank and insignia that shows his rank level and responsibility.

22. <u>Prison Police Ranks and Level of Authority</u>

1/ The ranks of the prison police shall be as follows:

a) Constable;

b) Assistant Sergeant;

c) Deputy Sergeant;

d) Sergeant;

e) Chief Sergeant;

f) Assistant Inspector;

g) Deputy Inspector;

h) Inspector;

i) Chief Inspector;

j) Deputy Commander;

k) Commander;

l) Assistant Commissioner;

m) Deputy Commissioner;

n) Commissioner;

o) Deputy Commissioner General; and

p) Commissioner General.

2/ The ranks of prison police officers specified under sub-article (1) of this Article with the exception of sub-article (o) and sub-article (p) shall have their respective insignia.

23. <u>Medals, Ribbons, Certificates and other prizes</u>

https://chilot.me

ኮሚሽነር ጄኔራሉ የላቀ ተግባር ለፈፀመ፣ አዲስ ግኝት ላስገኘ ወይም የሚያስመሰግን አገልግሎት ላበረከተ ፖሊስ ወይም ቡድን ሜዳይ፣ ሪባን፣የምስክር ወረቀት እና ሌሎች ሽልማቶች ይሰጣል።

፳፬. <u>የማረሚያ ፖሊስ የጡረታ መብት</u>

በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ለፖሊስ አባላት የተደነገገው የጡረታ መብት ለማረሚያ ፖሊስ አባላትም ተፈጻሚ ይሆናል።

፳፭. <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

፩/ የማረሚያ ፖሊስ የጡረታ መውጫ ዕድሜ:-

ሀ) ከኮንስታብል እስከ ዋና ሳጅን ማዕረግ ፶ ዓመት፣

ለ) ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር ማዕረግ ፶፪ ዓመት፣ እና

ሐ) ከዋና ኢንስፔክተር እስከ ኮሚሽነር ማዕረግ ፶፭ ዓመት፣

ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ለኮሚሽኑ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማረሚያ ፖሊስ አባል የአገልግሎት ዘመን ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ ከ፭ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት አንድ ማረሚያ ፖሊስ አባል የጡረታ መውጫ ዕድሜው ከደረሰ በኋላ የአገልግሎት ዘመኑን ማራዘም የሚቻለው:-

ሀ) የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባሉ ትምህርት፣ ልዩ እውቀትና ችሎታ ለኮሚሽኑ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፣"

ለ) የማረሚያ ፖሊስ አባሉን በደረጃ እድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ተተኪ ማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

ሐ)የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባሉ ለሥራ ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፣ እና

The Commissioner General shall award medals, ribbons, certificates and other prizes to a prison police officer or a group of prison police officers for outstanding accomplishment of missions, innovations or meritorious services.

24. <u>Prison Police Retirement Pension Rights</u>

The retirement pension rights provided for police officers under the public servants pension proclamation shall, mutatis mutandis be applicable to prison police officers.

25. <u>Retirement Age</u>

1/ The retirement age applicable to prison police officers shall be as follows:

a) for police officers having ranks from Constable to Chief Sergeant, 50 years;

b) for police officers having ranks from Assistant Inspector to Inspector, 52 years; and

c) for police officers having the ranks of Chief Inspector to Commissioner, 55 years.

2/ Notwithstanding sub-article 1 of this Article, where it becomes necessary for the Commission's work the retirement age of a prison police officer may be extended for a period not exceeding five years.

3/ the service of the prison police may be extended under sub Article 2 of this Article where:

a) his qualification, special skill and ability is found to be essential to the Commission;

b) it is not possible to replace him through promotion, transfer or recruitment.

c) he is proven fit for the service by medical certificate.

https://chilot.me

መ)የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባሉ አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ፣

ነው።

ክፍል አምስት
ስለ እስረኞች አያያዝ

ንዑስ ክፍል አንድ
የእስረኞች አቀባበል

፳፮.የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መኖሩን ስለማረጋገጥ

ማረሚያ ቤት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መኖሩን ሳያረጋግጥ ማንኛውንም ሰው መቀበል አይችልም።

፳፯. የመረጃ አያያዝ ሥርዓት

፩/ ማረሚያ ቤት እያንዳንዱን እስረኛ በተመለከተ በተሟላ ሁኔታ መረጃ የሚይዝበት ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ይኖረዋል።

፪/ ማረሚያ ቤት እስረኞችን ሲቀበል ወዲያውኑ የሚከተሉትን መረጃዎች መመዝገብ አለበት:-

ሀ) ሙሉ ስም፣ እድሜ፣ ዜግነት እና የቀድሞ አድራሻ፤

ለ) የታሰረበት የወንጀል ዓይነት ወይም ምክንያት እና መዝገብ ቁጥር፤

ሐ) ትዕዛዙን የሰጠው ፍርድ ቤት፤

መ) የቀጠሮ ቀን ወይም የፍርድ ልክ፤

ሠ) በማረሚያ ቤት የሚቆይበትን እና የሚፈታበትን ጊዜ፤

ረ) ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ ይዟቸው የመጣው ገንዘብ እና ንብረቶች ዝርዝር፤

ሰ) የቅርብ ቤተሰቦቹን ማንነትና አድራሻ፤

ሸ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ መሠረት የሚደረግ የሕክምና ምርመራ ውጤት፤

ቀ) ፎቶግራፍና የጣት አሻራ።

d) he has agreed to the extension of his service .

PART FIVE
TREATMENT OF PRISONERS

SECTION ONE
ADMISSION OF PRISONERS

26. Confirmation of Court Orders

No prison shall admit any person without insuring the issuance of an order or a decision by a competent court.

27. Record Keeping

1/ A prison shall have an up-to-date and modern record keeping system to maintain full information of each prisoner.

2/ A prison shall register the following information about the prisoner immediately upon admission:

a) full name, age, sex, nationality and prior address;

b) type of offence for which he is arrested or the reason for detention and the file number;

c) the court which issued the order;

d) court appointment date or the amount of penalty;

e) duration of stay in prison and date of release;

f) lists of money and property in possession of the prisoner upon admission;

g) identity of the prisoner’s close relatives and their address;

h) medical examination report as per the provisions of Article 28 of this Proclamation; and

i) a photo and finger prints.

https://chilot.me

፫/ እስረኛው በማረሚያ ቤት በሚቆይበትጊዜ የሚከተሉት መረጃዎች መመዝገብ አለባቸው፡-

ሀ) የፍርድ ሂደቱ ያላለቀ እንደሆነ የቀጠሮ ቀኖችን እና ክንውኖችን፤

ለ) ፀባይ እና ሥነ ምግባር ምዘና ውጤት፤

ሐ) የቀረበ አቤቱታ ካለ የቀረበበትን ቀን፣ ይዘት እና የተሰጠ መልስ ወይም ውሳኔ፤

መ)የቀረበ የዲሲፕሊን ክስ እና የተሰጠ ውሳኔ ወይም መልስ።

፬/ እስረኛው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መሠረት ከማረሚያ ቤት ሲለቀቅ የተፈታበት ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ተመዝግቦ ይያዛል።

፭/ በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፪) እስከ (፬) የተዘረዘሩት መረጃዎች በምስጢር ተጠብቀው እንዲያዙ በማድረግ ኮሚሽኑ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይይዛል፤ እስረኛው በጠየቀ ጊዜ መረጃዎቹን የማግኘት መብት አለው።

3/ The following information shall be recorded while the prisoner remains in prison:

a) when the court proceeding is in progress, appointment dates and what has been done in each appointment;

b) character and ethical character evaluation result;

c) when a complaint has been lodged, the date, content, response or decision made on the complaint; and

d) any disciplinary action instituted and a decision or response to such action.

4/ When the prisoner is released by a court decision or court order the hour, date, month and year of the release shall be registered.

5/ Without prejudice to what is provided for in other laws, the Commission shall ensure that information stated under sub-article (2) and sub-article (4) of this Article are kept confidential. It shall also keep other important information. The prisoner, upon his request, shall have access to the information.

፳፰. <u>የሕክምና ምርመራ</u>

ማረሚያ ቤት ማንኛውንም እስረኛ ሲቀበል በተቻለ መጠን ወዲያውኑ አጠቃላይ የህክምና ምርመራ በማድረግ በሚገኘው ውጤት መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፬ ላይ በተደነገገው መሠረት ተገቢውን ያከናውናል።

28. <u>Medical Examination</u>

A prison shall, to the extent possible immediately upon admission of a prisoner, undertake a general medical examination on the prisoner and based on the result, take appropriate action as per Article 34 of this Proclamation.

፳፱. <u>ቤተሰብን ስለማሳወቅ</u>

፩/ እስረኛ ወደ ማረሚያ ቤት እንደገባ ወዲያውኑ ስለሚገኝበት ቦታ ቤተሰቡን ወይም ጠበቃውን የማሳወቅ መብት አለው። እስረኛው ስለሚገኝበት ሁኔታ ለቤተሰቦቹ ወይም ጠበቃውን የሚያሳውቅበትን ሁኔታ ማረሚያ ቤት የማመቻቸት ግዴታ አለበት።

፪/ እስረኛው የውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ ስለታሰረበት ቦታ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኘው የሐገሩ ኤምባሲ

29. <u>Informing the Family</u>

1/ A prisoner shall have the right to inform his family or attorney about his situation immediately upon his admission. The prison shall facilitate the communication of the prisoner to his family or attorney about his situation.

2/ When the prisoner is a foreign national, the prison shall facilitate the necessary condition for the prisoner to inform his embassy or to an institution

https://chilot.me

ወይም የኤምባሲ አገልግሎት ለሚሰጥ ተቋም ወይም ለኢሚግሬሽን ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ እና ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያሳውቅ ማረሚያ ቤት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለበት።

providing Embassy services or to the Immigration, Nationality and Vital Events Agency and Ministry of Foreign Affairs of FDRE.

፫/እስረኛው ዜግነት ከሌለው ወይም የሚገኝበት ሀገር በኢትዮጵያ ውስጥ ኤምባሲ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ከሌለ እስረኛው አገልግሎቱን አገኛለሁ ብሎ ለጠቆመው ሀገር ኤምባሲ ወይም ይህም ከሌለ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮ ላላቸው ተመሳሳይ አገልግሎት ሊሰጡ ለሚችሉ አለም አቀፍ ተቋሞች እና ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያሳውቅ ማድረግ አለበት።

3/ When the prisoner is stateless or his country does not have an embassy or an institution providing embassy services in Ethiopia, the prison shall allow the prisoner to inform an embassy of his choice or to an international institution with an office in Ethiopia providing similar services and Ministry of Foreign Affairs of FDRE.

፬/ ማረሚያ ቤት እስረኛው ስለሚገኝበት ቦታ እና ሁኔታ በቤተሰቡ፣ በጠበቃው ሲጠየቅ በማንኛም ቢሆን ትክክለኛውን መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት።

4/ A prison shall, when requested by the family or attorney about the whereabouts of the prisoner, provide correct information in all cases.

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ እስረኛ የመፈቻ ጊዜው በሚደርስበት ጊዜ ማረሚያ ቤቱ መረጃ ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ ማስረከብ አለበት።

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) and (3) of this Article, the prison shall hand over information about the release time of the foreigner prisoner to the Immigration, Nationality and Vital Events Agency.

፴. <u>መብት እና ግዴታዎችን ስለማሳወቅ</u>

ማረሚያ ቤት እስረኛውን ሲቀበል በማረሚያ ቤት በሚቆይበት ጊዜ ስላሉት መብቶች እና ግዴታዎች የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

30.<u>Informing Rights and Obligations</u>

Upon admission, the prison shall inform prisoners of their rights and duties during their stay in a prison.

፴፩. <u>እስረኛ ወደ ማረሚያ ቤት ይዞ ስለሚገባው ገንዘብና ንብረቶች</u>

31. <u>Money and Property that can be Brought to Prison</u>

፩/ ኮሚሽኑ የተጣለበትን እስረኞችን የመጠበቅ እና የማረም ኃላፊነት እንዲሁም የእስረኞችን መብቶች ባገናዘበ መልኩ እስረኛ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲያስገባ የተፈቀዱ እና የተከለከሉ ንብረቶች ዝርዝር ያዘጋጃል። ይኼንኑ በቅበላ ወቅት ለእስረኞች ያሳውቃል።

1/ The prison shall, taking into account the Commission's responsibility to protect and rehabilitate prisoners as well as the rights of the prisoner, prepare a list of property that can be brought to prison by a prisoner. The prison shall, during admission, inform the prisoner about the list.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት

2/ The prison shall, based on the list prepared under

https://chilot.me

ባዘጋጀው ዝርዝር መሠረት እንዳይገቡ የተከለከሉ የእስረኛዉ ገንዘብና ንብረቶች ዝርዝር የያዘ ሰነድ በማዘጋጀት እስረኛውና የተረከበው የፖሊስ አባል እንዲፈርምበት በማድረግ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ በማስቀምጥ ለተወካዩ ይሰጣል ወይም ሲፈታ መልሶ እንዲወስድ ያደርጋል።

ንዑስ ክፍል ሁለት
ስለ እስረኞች አያያዝ

፴፪.አጠቃላይ መርሆዎች

፩/ እስረኛ በማረሚያ ቤት ቆይታው ሰብአዊ መብቱን፣ ክብሩን እና ጤንነቱን ያከበረ አያያዝ የማግኘት መብት አለው።

፪/ እስረኛ ሰብአዊ ክብሩን ከሚያዋርድ፣ ጭካኔ ከተሞላበት እና ጤንነቱን አደጋ ላይ ከሚጥል አያያዝ የመጠበቅ መብት አለው።

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእስረኞችን አያያዝ በተመለከተ በዕድሜ፣ በዜግነት፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በታሰረበት ምክንያት፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ወይም በሌሎች ማናቸውም መሰል ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው፡

፬/ ኮሚሽኑ የዘረጋቸው የአሠራር ሥርዓቶች፣ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ወይም የሚፈፅማቸው ተግባሮች ዋና ዓላማ እስረኞች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ታርመው እና በመልካም ሥነ ምግባር ታንፀው ህግ አክባሪ፣ ሠላማዊ እና አምራች ዜጎች ሆነው ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ማድረግ አለበት።

፴፫.እስረኞችን ለይቶ ስለመያዝ

ማረሚያ ቤት በዕድሜ፣ በእስር ምክንያት፣ወይም የጤንነት ሁኔታን መሠረት በማድረግ ፡-

sub-article (1), prepare a document listing the money and property in the possession of the prisoner that cannot be brought to prison, have it signed both by the officer and prisoner, and keep the money and property in a safe place and hand over them to the prisoner's representative or to the prisoner upon his release.

SECTION TWO
TREATMENT OF PRISONERS

32. General Principle

1/ A prisoner shall have the right to be treated during his stay in prison with full respect of his rights, dignity and health.

2/ A prisoner shall have the right to be protected from degrading, inhumane and cruel treatment or from treatment that endangers his health.

3/ Without prejudice to Article 34 of this Proclamation there shall be no discrimination on the treatment of prisoners based on gender, age, nationality, ethnicity, language, reason for detention, religion, political opinion, economic and social conditions, or any other similar conditions.

4/ The main objective of the administrative procedures set by the Commission, the decisions it makes or activities it undertakes shall be to ensure that prisoners will return to the community rehabilitated and ethically sound, law abiding, peaceful and productive citizens.

33. Separate Accommodations for Prisoners

Based on reason for detention, gender, age, or health conditions the prison shall designate separate quarters for:

https://chilot.me

፩/ሴቶችን ከወንዶች፤

፪/ ፍርደኞችን በፍርድ ሂደት ላይ ከሚገኙ፤

፫/ በፍትሐ ብሔር እና በደንብ መተላለፍ ምክንያት የታሰሩትን ከሌሎች እስረኞች፤

፬/ ወጣቶችን ከአዋቂ እስረኞች፤

፭/ ከፍተኛ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ከሌሎች እስረኞች፤

በተለየ ቦታ እንዲኖሩ ማድረግ አለበት።

1/ male from female;

2/ persons detained upon judicial remand from convicted prisoners;

3/ detainees of civil proceedings or on violation of petty offences from other prisoners;

4/ juveniles from others; and

5/ persons that require high security from others.

፴፬. <u>የመኖሪያ እና የመኝታ አገልግሎት አሰጣጥ</u>

፩/ እስረኛ በማረሚያ ቤት ቆይታው ሰብአዊ መብቱን፣ ክብሩን፣ ደህንነቱን እና የጤንነቱን ሁኔታ የጠበቀ መኖሪያ ሊኖረው ይገባል።

፪/ ማረሚያ ቤት በስታንዳርዱ መሰረት አንድ የመኖሪያ ክፍል ሊይዝ ከሚችለው ቁጥር በላይ እስረኞች እንዲኖሩት ማድረግ የለበትም።

፫/ እስረኞች የሚኖሩበት ቦታ ሰብአዊ ክብራቸውን፣ ግላዊነታቸውን እና ጤንነታቸውን ያገናዘቡ በቂ እና ንፅህናቸው የተጠበቀ የንፅህና መጠበቂያ፣ የመታጠቢያ እና የመፀዳጃ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል።

፬/ ማረሚያ ቤት ለእያንዳንዱ እስረኛ ንጽህናው የተጠበቀ አልጋ፣ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ ማቅረብ አለበት።

34. <u>Provision of Accommodation</u>

1/ A prisoner shall have an accommodation that preserves his human rights, dignity, security and health during his stay in prison.

2/ The prison shall ensure that a prison room is not occupied by prisoners beyond its standard capacity.

3/ The place where prisoners live shall have sufficient and clean personal hygiene, bathing and toilet facilities considering their personal dignity, privacy and health.

4/ The prison shall provide clean bed, mattress, blanket and bed sheet to each prisoner.

፴፭.<u>አልባሳት</u>

፩/ ኮሚሽኑ እስረኞችን የመጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት፣ የማረሚያ ቤትን ሥርዓት እና ደንብ ለማስከበር እንዲሁም ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ላይ የተመለከተውን አመዳደብ መሠረት ባደረገ መልኩ እስረኞች የተለ ያዩ ዩኒፎርም እንዲለብሱ ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግል ልብሳቸውን እንዲለብሱ ሊፈቅድ ይችላል።

35. <u>Clothing</u>

1/ The Commission shall, for the purpose of discharging its responsibilities to protect prisoners, enforce orders and administrative regulation and ensure security, provide different uniforms to prisoners based on the classification under Article 33 of this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article when necessary the Commission may allow prisoners to wear their own clothing.

https://chilot.me

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም እስረኛ በማረሚያ ቤት ቆይታው የግል የውስጥ አልባሳቱ አጠቃቀም ላይ ገደብ መጣል አይቻልም።

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article no limitation can be imposed on use of private underwear.

፴፮.<u>የምግብ አቅርቦት</u>

36. <u>Provision of Food</u>

፩/ ማረሚያ ቤት ለእያንዳንዱ እስረኛ ጤንነቱን እና አካላዊ ብቃቱን ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ በቀን ሦስት ጊዜ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

1/ The prison shall provide, three times a day, sufficient and balanced diet for each prisoner sufficient to preserve his health and his physical fitness.

፪/ ኮሚሽኑ የሚያቀርበው ምግብ አቅም በፈቀደ መጠን የእስረኛውን ሐይማኖት፣ ባህልና ሌሎች ሁኔታዎችን ያገናዘበ ይሆናል።

2/ The meal to be provided by the Commission shall, to the extent possible consider the religion, culture and other circumstances t of the prisoner.

፫/ እስረኛው በቂ የሆነ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲያገኝ መደረግ አለበት።

3/ Sufficient and clean drinking water shall be made available to prisoners.

፬/ ማረሚያ ቤት በጤናው ሁኔታ በተረጋገጠ የሐኪም ትዕዛዝ ልዩ ምግብ ያስፈልገዋል ለተባለ እስረኛ በሐኪም ትዕዛዝ መሠረት ምግብ ያቀርባል።

4/ A prisoner with a health problem shall be provided with a special food based on recommendation by a medical officer.

፭/ የምግብ አዘገጃጀት እና የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች ደረጃቸውን እና ንጽህናቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው።

5/ Food preparation and kitchens shall be clean and up to standard.

፮/ ማረሚያ ቤት የእስረኞችን ደህንነት፣ የማረሚያ ቤትን ደንብ እና ሥርዓት ለማስከበር የሚተገብራቸው ምክንያታዊ የቁጥጥር ሥርዓቶች እንደተጠበቁ ሆነው እስረኛ ከቤተሰቦቹ ወይም ከዘመዶቹ የሚመጡለትን ምግቦች እና አልኮልነት የሌላቸው መጠጦች ማረሚያ ቤት ለማስገባት መብት አለው። ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

6/ Without prejudice to the reasonable inspection procedures in place to protect the safety of prisoners and enforcement of prison administrative regulations, a prisoner shall have the right to receive food and non-alcoholic drinks from his family or relatives. Particulars shall be determined by Regulation.

፯/ ማረሚያ ቤት እንደ አመቺነቱ ተመጣጣኝ በሆነ ክፍያ የምግብና አልኮልነት የሌላቸው ቀዝቃዛና ትኩስ መጠጦችን እንዲያገኙ ሊያመቻች ይችላል።

7/ The prison may, as appropriate, facilitate the availability of food as well as non-alcoholic hot and cold drinks at the prison for a reasonable price.

፴፯. <u>የሕክምና አገልግሎት</u>

37. <u>Medical Services</u>

፩/ የሀገሪቱ የጤና አጠባበቅ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት ሌሎች ዜጎች የሚያገኙትን የህክምና አገልግሎት እስረኞች በነፃ የማግኘት መብት አላቸው።

1/ Prisoners shall have access to free medical services available to all other citizens pursuant to health service laws of the country.

https://chilot.me

፪/ ኮሚሽኑ በማረሚያ ቤት ውስጥ ለእስረኞች የተሟላ የ፳፬ ሰዓት የህክምና አገልግሎት መስጠት እንዲችል ብቃት ባላቸው የህክምና ባለሙያዎች ቡድን፣ በቂ የህክምና መሳሪያዎችና የመድሀኒቶችን አቅርቦት በማሟላት ደረጃውን የጠበቀና መሰረታዊ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ የጤና ተቋም ያደራጃል።

2/ The Commission shall establish a medical center in the prison with qualified medical personnel, sufficient medical facility and sufficient medicine supply that can provide medical services to the prisoners for 24 hours.

፫/ የማረሚያ ቤት የጤና ተቋም የባለሙያዎች ቡድን የጠቅላላ ሕክምና፣ የሥነ-አዕምሮ እንዲሁም የሥነ-ልቦና ባለሙያዎችን ያካተተ መሆን አለበት።

3/ The medical team at the prison medical center shall consist of professionals on general health care, mental health and psychiatry.

፬/ በኮሚሽኑ ሥር የሚገኙ የጤና ተቋም ባለሙያዎች የሙያውን ሥነ ምግባር፣ ሙያውን በተመለከተ ግዥ የሆኑ የሐገሪቱ ሕጎች እና ደንቦች እንዲሁም በዚህ አዋጅ ላይ የተደነገጉትን አጠቃላይ መርሆች ባከበረ መልኩ ለእስረኞች የሕክምና አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

4/ Professionals at the prison medical center shall have the responsibility to provide medical services in conformity with their professional ethics, laws and regulations of the country governing the professions as well as the general principles enshrined under this Proclamation.

፭/ የእስረኞች አያያዝ፣ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም የማረሚያ ቤት አካባቢያዊ ሁኔታ በእስረኞች ወይም በኮሚሽኑ ሠራተኞች ላይ የጤና ችግር የሚያስከትል አለመሆኑ መረጋገጥ አለበት።

5/ The Commission shall ensure that the treatment of prisoners, provision of services as well as the prison environment do not create health problems for prisoners or the employees of the Commission.

፮/ በማረሚያ ቤት ጤና ተቋም ሥር የሚገኙ ባለሙያዎች በየጊዜው አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን፣ የአገልግሎቶችን አሰጣጥ፣ የእስረኞችን አያያዝ እንዲሁም የማረሚያ ቤትን አካባቢያዊ ሁኔታ በመጎብኘት ወይም በመፈተሽ የጤና ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን በመለየት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለማረሚያ ቤት ያሳውቃሉ።ማረሚያ ቤቱም በፍጥነት ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል።

6/ The medical professional at the prison medical center shall from time to time visit facilities providing services, the provision of services, the treatment of prisoners as well as the prison environment; identify issues that may cause health problems and inform same to the prison to take corrective actions. The prison shall take corrective measures on issues so identified forthwith.

፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ ላይ በተደነገገው መሠረት በሚያደርገው የሕክምና ምርመራ ውጤት መነሻነት ልዩ የሕክምና ክትትል

7/ When, based on the medical examination undertaken as per Article 28 of this Proclamation, there are prisoners that need special medical follow up or inflicted by communicable diseases that can impair

https://chilot.me

የሚያስፈልጋቸው ወይም ሌሎች እስረኞች ላይ ለጤና ችግር በሚዳርግ ተላላፊ በሽታ የተጠቁ እስረኞች ካሉ ማረሚያ ቤት ለእነዚህ እስረኞች የተለየ ቦታ በማዘጋጀት የሕክምና አገልግሎቱን እንዲያገኙ ያደርጋል።

the health of other prisoners, the prison shall prepare a separate place where such prisoners will continue to get the medical services.

፰/ እስረኛ የጤና ችግር ሲያጋጥመው ወይም የሕመም ስሜት ሲሰማው በማንኛውም ሰዓት በማረሚያ ቤት ውስጥ በሚገኝ የጤና ተቋም ተገቢውን የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አለው።

8/ A prisoner who encounters a medical problem or feels ill shall have the right to get proper medical service at a medical center in the prison at any time.

፱/ በማረሚያ ቤት የጤና ተቋም የሕክምና አገልግሎት እያገኘ ያለ ወይም ለማግኘት የጠየቀ እስረኛ የጤና ሁኔታ በጤና ተቋሙ ከሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት አቅም በላይ የሆነ ሕክምና የሚጠይቅ ከሆነ ኮሚሽኑ በጤና ተቋሙ ባለሙያዎች በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ወዲያውኑ ተገቢውን ጥበቃ በመመደብ እስረኛው ያስፈለገውን የሕክምና አገልግሎት ሊሰጥ ወደሚችል የመንግሥት ሆስፒታል በመውሰድ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያደርጋል።

9/ When the health condition of a prisoner, who has been getting medical service or has requested to get such services at the prison medical center, requires medical services that are beyond the capacity of the prison medical center, the Commission shall, based on a medical report presented to it by the medical professionals, ensure that the prisoner gets the required medical service at the appropriate public hospital under escort.

፲/ የሕክምና አገልግሎት እያገኘ ያለ ወይም አገልግሎቱን ለማግኘት የጠየቀ እስረኛ ከሕክምና ባለሙያዎች ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው። ይሁን እንጂ በእስረኛው እና ከሕክምና ባለሙያዎች ጋር የሚደረገውን ንግግር መስማት በማያስችል ወይም በሕክምና ባለሙያዎች የሚከናወኑ የሕክምና አሰጣጥ ድርጊቶችን መለየት በማያስችል እይታ ርቀት ውስጥ በመገኘት የማረሚያ ቤት ፖሊስ ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ ይሠራል።

10/The communications of a prisoner who has been getting medical services or has requested to get such services at the prison medical center with medical professionals shall be kept confidential. However, a prison police officer shall perform the necessary surveillance activity from a distance that does not allow him to hear the communications between the prisoner and the medical professional or does not allow him to identify the medical service being provided to the prisoner by the medical professionals.

፲፩/ በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእስረኛ የሕክምና መረጃዎች ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ነው።

11/ Without prejudice to the provisions of other relevant laws the medical information of a prisoner shall be kept confidential.

፲፪/ ኮሚሽኑ አቅም በፈቀደ መጠን የመንግሥት

12/The Commission shall, to the extent possible,

https://chilot.me

ወይም የግል የጤና ተቋማት ጋር ወይም መሰል አገልግሎት ከሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለእስረኞች እንዲሁም ለማረሚያ ቤት ሠራተኞች ስለ አጠቃላይ የጤና አጠባበቅ ሁኔታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እና ስልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፴፰. <u>የሃይማኖት እና እምነት ነፃነት</u>

፩/ እስረኛ በማረሚያ ቤት ቆይታው የሃይማኖት እና እምነት ነፃነቱ የተጠበቀ ነው።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም እስረኛ ሐይማኖቱን ወይም እምነቱን ሲያራምድ የሌሎችን ሐይማኖትና ዕምነት በማያውክና ክብር በማይነካ መልኩ መሆን አለበት።

፫/ ማንኛውም እስረኛ ሐይማኖቱንና ዕምነቱን ሲያራምድ በማረሚያ ቤቱ የተጣሉ የደህንነትና የቁጥጥር ደንብና መመሪያዎችን ማክበር አለበት።

፴፱. <u>ስፖርታዊና አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና መዝናኛ</u>

፩/ በማረሚያ ቤት ግቢ ውስጥ በግል ወይም በቡድን እስረኛ ለጤንነቱ ተስማሚ የሆነ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን የማድረግ መብት አለው።

፪/ ኮሚሽኑ በማረሚያ ቤት ግቢ ውስጥ አካላዊ እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉበት በቂ የሆነ ክፍት ቦታ ያዘጋጃል።

፫/ ኮሚሽኑ ከውጭው ማህበረሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር በተቻለ መጠን ለእስረኞች የባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስፖርታዊ እና መሰል የመዝናኛ መሰናዶ ያዘጋጃል።

፵. <u>ከውጪው ማህበረሰብ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት</u>

ኮሚሽኑ የማረሚያ ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት በማስጠበቅና ኃላፊነቱን በመወጣት የማረምና ማነፅ

facilitate the provision of general health care awareness creation education or training programs for prisoners and employees of the prison by establishing contacts with public or private medical institutions or non-governmental organizations providing similar services.

38. <u>Freedom of Religion and Belief</u>

1/ A prisoner shall have freedom of religion and belief during his stay in prison.

2/ Withstanding Sub Article 1 of this provision, all religious and spiritual practice shall observe other religions and beliefs and should be respectful and none degrading to others;

3/. where practicing ones religion and belief all prisoners shall observe rules andregulations put forward to maintain safety and order.

39. <u>Sports, Physical Exercise and Recreation</u>

1/ Prisoners, individually or in group, shall have the right to engage in physical exercises appropriate to their health within the compound of the prison.

2/ The Commission shall arrange a sufficient open space within the prison compound for sports and physical exercises.

3/ The Commission shall, to the extent possible and in collaboration with the community outside prison, prepare cultural, social, sports and other similar events for the prisoners.

40. <u>Relation with Outside Community</u>

Without prejudice to the limitations and inspection procedures put in place to protect prisoners and enforcement of prison administrative regulations, as

https://chilot.me

ተግባሩን ለማሳደግ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሚዘረጉ የቁጥጥር ሥርዓቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለእስረኛው የሚከተሉት መብቶች ይከበሩለታል፡-

፩/ በማረሚያ ቤት ቆይታው ከትዳር አጋሩ፣ ከዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቹ፣ ከሐኪሞቹ እና ከሕግ አማካሪዎቹ ጋር በአካል ወይም በጽሑፍ የመገናኘት መብት አለው፤

፪/ ከቤተሰቡ፣ ከሙያ እና እምነት አማካሪዎቹ፣ ተቋማት ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ወይም የደብዳቤ ልውውጦች ላይ ተግባራዊ የሚደረገው ምክንያታዊ የቁጥጥር ሥርዓት እንደተጠበቀ ሆኖ ምስጢራዊነታቸው የተጠበቀ ነው፤

፫/ በማረሚያ ቤት ቆይታ የመንግሥት ወይም የግል የህትመት ውጤቶችን በራሱ ወጪ ወደ ማረሚያ ቤት በማስገባት ወይም በሚኖሩበት ቦታ በሚያዘጋጃቸው የድምፅ እና የምስል መረጃ ማሰራጫ መሣሪያዎች የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን በመከታተል ስለውጪው ህብረተሰብ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን የማግኘት መብት አለው፤

፬/ ማረሚያ ቤቱ የግንኙነቱን ምሥጢራዊነት ለማረጋገጥ አቅም በፈቀደ መጠን እስረኞች ከጎብኝዎቻቸው ጋር የሚገናኙበት እና ቆይታ የሚያደርጉበት በቂ ስፋት ያለው ቦታ ያዘጋጃል፤

፭/በጽኑ የታመመ እስረኛ ጎብኝዎቹ ወዳለበት የመኖሪያ ክፍል ወይም የሕክምና ተቋም ውስጥ ገብተው እንዲጎበኙት ይደረጋል፤

፮/ የመፈቻ ጊዜያቸው የተቃረበ እስረኞች ከማረሚያ ቤት ውጭ እንዲሠሩ በማድረግ፣ በራሳቸው ወይም በአጃቢ ወጥተው እንዲመለሱ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ከውጪው ማህበረሰብ ጋር አስቀድመው ግንኙነት የሚፈጥሩበት ሥርዓት በማረሚያ ቤቱ ይዘረጋል።

፵፩. <u>ስለ እስረኞች ፈቃድ</u>

well as to protect the safety of the prison community and enhance the effectiveness of its rehabilitation efforts, a prisoner, during his stay in prison shall have:

1/ have the right communicate in person or in writing with his spouse, relatives, friends, religious counselors, medical advisors and legal advisors.

2/ have the right to keep his communications with his family, professional and religious advisors, institutions or other individuals confidential subject to reasonable inspection procedures.

3/ have the right to get up to date information about the community outside prison by bringing to the prison public or private press resources at his own expense, or by following up audio and video programs made available at the prison.

4/ to ensure the confidentiality of communications, the prison shall prepare sufficient place where prisoners can meet and stay with their visitors to the extent resources allow.

5/ visitors of a seriously ill prisoner shall be allowed to visit him in his room or at the medical center.

6/ the prison shall establish a system whereby a prisoner who is close to completing his term of imprisonment is able to start communicating with the community outside prison by allowing him to work outside the prison, to go out of prison and come back with or without escort or through any other mechanism.

41. <u>Permission for Prisoners</u>

https://chilot.me

፭/ ኮሚሽኑ እስረኞችን የመጠበቅ፣ የማረሚያ ቤትን ደንብ እና ሥርዓት ማስከበር እንዲሁም የማረሚያ ቤትን ማህበረሰብ ደህንነት በማስጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚጥላቸው ገደቦች እና የሚዘረጋቸው የቁጥጥር ሥርዓቶች እንደተጠበቁ ሆነው እስረኛው በውክልና ሊያከነዉናቸው የማይችላቸውን ማህበራዊ ጉዳዮች ሲኖሩ ኮሚሽኑ እንደሁኔታው በመንግሥት የሥራ ሰዓት ለእስረኛው ፈቃድ የሚሰጥበት አሰራር ይዘረጋል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቅርብ ቤተሰቡ በሞት የተለየ እንደሆነ ማረሚያ ቤቱ ባለበት ከተማ ውስጥ ፈቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል። አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

ንዑስ ክፍል ሦስት
የማረም፣ ማነጽ እና ተሐድሶ አገልግሎት

፵፪. የማህበራዊና የምክር አገልግሎት

፩/ ታራሚዎች ወደ ማረሚያ ቤት ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በግል፣ በቡድንና አቻ ለአቻ በሚሰጥ የምክር አገልግሎት የሥነ-ልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል።

፪/ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የማህበራዊ አኗኗር እና የሕይወት ክህሎት እንዲያዳብሩ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል።

፫/ ታራሚዎች የንቃተ ሕግ፣ የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት የሕግ የበላይነትን እንዲረዱ ይደረጋል።

፵፫. የቀለምና የሙያ ስልጠና

፩/ ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የግል ፍላጎቱን መሠረት ባደረጉ የትምህርት ፕሮግራሞች እና ስልጠናዎች ላይ በመሳተፍ ዕውቀቱን እና ክህሎቱን የማሻሻል መብት አለው።

፪/ ኮሚሽኑ ታራሚ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጸ፣

1/ Without prejudice to the limitations and inspection procedures put in place to protect prisoners and enforcement of prison administrative regulations, as well as to protect the safety of the prison community, where there are social activities that the prisoner cannot perform through a representative, the Commission shall establish a system through which the prisoner can get permission as appropriate during public working hours.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this article, in case of death of a close relative a prisoner shall be given permission in the town where the prison is located. Particulars shall be determined by regulation.

SECTION THREE
CORRECTION AND REHABILITATION

42.Social and Counseling Services

1/Prisoners shall, through individual, group and peer confidential consultation services, get psychological assistance from the time of their admission to prison.

2/ Prisoner shall be given support to develop social life and skills during their stay in prison.

3/Prisoners shall be given legal awareness, civic and ethics education to understand the rule of law.

43. Academic and Vocational Training

1/ A prisoner shall have the right to improve his knowledge and skills by participating in educational and training programs based on his interest during his stay in the prison.

2/The Commission shall, with a view to ensure that

https://chilot.me

አምራች እና ብቁ ዜጋ ሆኖ ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀል ለማድረግ ታራሚው ከማረሚያ ቤት ሲወጣ ወደ ፊት ለሚመራው ህይወት ጠቃሚ በሆኑ የትምህርት ወይም የልዩ ሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፍ ያደርጋል።

፫/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀውን ኃላፊነቱን ለመወጣት ከመንግሥት እና የግል ትምህርት ተቋማት ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር እነዚህ ተቋማት በርቀት ትምህርት ፕሮግራሞቻቸው ወይም እንደሁኔታው በማረሚያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ለታራሚዎች የትምህርት ወይም የሙያ ስልጠና የሚሰጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፬/ ማንኛውም ማንበብና መጻፍ የማይችል ታራሚ የመማር ግዴታ አለበት።

፭/ ኮሚሽኑ በእያንዳንዱ ማረሚያ ቤት በበቂ የአጠቃላይ እውቀት እና የመዝናኛ መፅሐፍት የተደራጀ ቤተ መፅሐፍት ያደራጃል፤ ታራሚዎች መፅሐፍትን እንዲያነቡና እንዲጽፉ ያበረታታል።

፮/ ኮሚሽኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚያወጣ ደንብ መሠረት ሊኖር የሚገባው ምክንያታዊ ቁጥጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ታራሚው የፈለገውን መፅሐፍ ወደ ማረሚያ ቤት በማስገባት የማንበብ መብት አለው።

፵፬.ስለ መልሶ ማቋቋም

ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በማህበር በማደራጀትና በልማት ሥራዎች በማሳተፍ የሥራና የቁጠባ ባህል እንዲያዳብሩ በማድረግ ምርታማ ዜጎች እንዲሆኑ ይደረጋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

፵፭.በሥራ ስለመሰማራት

፩/ ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው ሥራ የመሥራት መብት አለው።

፪/ ማረሚያ ቤት በሌሎች አግባብነት ባላቸው

prisoners join society as ethically rehabilitated, productive and capable citizens, organize educational or special professional training programs for each prisoner that are relevant to his life.

3/ The Commission, to discharge its responsibilities stated under sub-article 2 of this Article, shall establish relations with public and private education institutions or other institutions providing similar services and create suitable conditions for the institutions to provide education or special professional trainings for the prisoners within the premises of the prison or through distance education programs.

4/ any prisoner who is unable to read and write shall have the obligation to learn.

5/ The Commission shall organize a library with sufficient general knowledge and recreational books in each prison and shall encourage the prisoners to read books.

6/ Without prejudice to reasonable inspection by the Commission based on a Regulation to be issued to implement this proclamation, a prisoner shall have the right to bring to prison and read any book of his choice.

44. Rehabilitation

Prisoners shall be made productive citizens by developing working and saving culture through organizing them in associations and engaging them in developmental activities. Particulars shall be determined by a directive.

45. Work Assignments

1/ A prisoner shall have the right to work during his time in prison.

2/ Without prejudice to relevant laws of the country on

https://chilot.me

የሀገሪቱ ሕጎች ስለ ሥራ ቦታ ደህንነት የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ውጤት ባላቸው ሥራዎች ላይ በተመጣጣኝ ክፍያ እንዲሳተፉ ማስገደድ ይችላል። የጋራ አገልግሎት የሚሰጥባቸው የመኖሪያ ቤት፣ ግቢ፣ የቤተሰብ መጎብኛ እና የመሳሰሉትን ቦታዎች የማጽዳት ሥራ ክፍያ አይከፈልም።

work place safety, the prison can compel prisoners to participate in productive works against a reasonable payment. No payment shall be made for cleaning common service areas like cell, compound, visiting areas and other places.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃደኛ ያልሆኑ ተከሳሾች ወይም በፍትሐ ብሔር ትዕዛዝ የታሰሩ እና በዕድሜ የገፉ ታራሚዎች እንዲሰሩ አይገደዱም።

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, persons on remand or detainees of civil proceedings or prisoners at advanced age shall not be compelled to work.‹

፬/ ማረሚያ ቤት ከመንግሥት እና የግል ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር እነዚህ ተቋማት የታራሚዎች የሥራ ውጤት የሆኑትን ምርት በቋሚነት የሚገዙበትን ወይም እንደሁኔታው የገበያ ትስስር በመፍጠር ገቢ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል፣ ከሚገኘውም ገቢ በሥራው ወይም በአገልግሎቱ የተሳተፉ ታራሚዎች ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲያገኙ ያደርጋል።

4/ The prison may earn income by establishing relations with public and private institutions that can buy the products of the works of the prisoners on a regular basis or by creating market chains as appropriate. The prisoners who participated in the work or service shall be entitled to proportional payment from the income.

፭/ ታራሚዎች የሚሳተፉበት ሥራ ወይም አገልግሎት አሰጣጥ የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ወደ ሕብረተሰቡ ሲቀላቀሉ ለሚመሩት ሕይወት ጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

5/ The work or service where the prisoners participate shall be useful to the life of the prisoner when they join the community upon completion of their imprisonment.

፵፮.ታራሚዎችን ስለማዛወር

46. Transfer of Prisoners

፩/ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ እስረኛ ቤተሰቦቹ ወደ ሚኖሩበት አካባቢ ወይም ከፌዴራል ወደ ክልል ወይም ከክልል ወደ ፌደራል ማረሚያ ቤት እንዲሁም ከአንዱ ፌዴራል ማረሚያ ቤት ወደ ሌላው ለመዛወር ከጠየቀ በኮሚሽኑ ታይቶ ሲፈቀድ ሊዛወር ይችላል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

1/ A prisoner who has received a final court verdict may ask to be transferred to a prison where his family live or to be transferred from a federal to regional or from regional to federal or from one federal to another federal prison and may be transferred to such prison upon the approval of the Commission. Particulars shall be determined by Regulation.

፪/ ታራሚ ከታሰረበት ተቋም ወደ ሌላ ተቋም መዛወሩን አመቺ በሆነ መንገድ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚፈልገው ሰው የማሳወቅ መብት

2/ A prisoner shall have the right to inform his family or any other person about his transfer to another prison in a way convenient to him.

https://chilot.me

አለው።

ንዑስ ክፍል አራት
የደህንነት ጥበቃ ሥርዓቶች

፵፯. የጥበቃ እና ቁጥጥር አስፈላጊነት

ማረሚያ ቤት የእስረኞቹን እና የማረሚያ ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ፣ የማረሚያ ቤትን ደንብና ሥርዓት ለማስጠበቅ እንዲሁም ፀጥታው የተከበረ ሰላማዊ የማረሚያ ቤት አካባቢ እንዲኖር ለማድረግ አስፈላጊ የሆነ የጥበቃ እና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል። የዲስፕሊን እርምጃዎች ይወሰዳል።

፵፰. የስጋት ደረጃዎችን ስለመለየት

፩/ ማረሚያ ቤት እስረኞችን እንደተቀበለ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እስረኛ ፀባይ፣ የቀድሞ ታሪክ፣ የታሰረበትን ምክንያት፣ በማረሚያ ቤት የሚቆይበትን የጊዜ ርዝመት፣ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማጥናት እስረኛው በማረሚያ ቤት ቆይታው ከእስር ቤት ለማምለጥ፣ በሌሎች እስረኞች እንዲሁም የማረሚያ ቤት ሠራተኞች ላይ ጉዳት ለማድረስ፣ ፀጥታ እና ሰላምን ለማደፍረስ፣ የማረሚያ ቤትን ደንብ እና ሥርዓት ለመጣስ፣ በንብረት ላይ እንዲሁም በራሱ ላይ ጉዳት ለማድረስ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተውን የስጋት ደረጃ በመለየት በከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ይመድባል።

፪/ ማረሚያ ቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የስጋት ደረጃዎችን ከለየ በኋላ ከስጋት ደረጃው ጋር ተመጣጣኝ የሆነውን የጥበቃ እና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ይተገብራል።

፫/ ማረሚያ ቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ በተመለከተው መሠረት የሚያወጣቸውን የስጋት ደረጃዎች በየጊዜው በመገምገም እስረኞቹ የተመደቡበትን የስጋት ደረጃ ያሻሽላል።

SECTION FOUR
SECURITY PROTECTION PROCEDURES

47. Need for Security and Inspection

The prison shall establish the necessary security and inspection system and shall take disciplinary measures to protect the safety of the prisoners and the prison community, to enforce prison administrative regulations as well as to create a secure and peaceful prison environment.

48. Identification of Risk Levels

1/ The prison shall, within a certain period of time after admission of prisoners, study the character, past history, reason for detention, period of time in prison and other related conditions in relation to each prisoner and assign them as high risk, medium risk and low risk by identifying the potential risk of each prisoner to escape from prison, to inflict harm on other prisoners and the prison employees, breaking security and peace, breaching prison administrative regulations, inflicting harm on property and on himself.

2/ The prison shall, based on the identified risk levels under sub-article (1) of this article, establish security and inspection procedures commensurate with the risk levels.

3/ The prison shall regularly evaluate the risk levels as stipulated under sub article 1 of this Article and change the risk levels assigned to the prisoners

https://chilot.me

፶፱.አካላዊ፣ የንብረት እና የመኖሪያ ቦታ ፍተሻ

፩/ ማረሚያ ቤት በዚህ አዋጅ የተጣለበትን እስረኞችን የመጠበቅ፣ የማረሚያ ቤትን ሰላምና ፀጥታ የማስከበር፣ የማረሚያ ቤትን ማህበረሰብ ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት ብቻ ለጉብኝት የሚመጡ ሰዎችን፣ ወደ ማረሚያ ቤት በሚገቡ መገልገያ እቃዎች ወይም ምግቦች እና መጠጦች እንዲሁም እስረኞች በሚኖሩበት፣ በሚሠሰሩበት ወይም በሚተኙበት ቦታዎች ላይ ፍተሻዎችን ያደርጋል።

፪/ ማረሚያ ቤት የሚያደርገው ፍተሻ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የእስረኞቹን ወይም የጎብኝዎችን ክብር የሚያዋርድ ወይም የግላዊነት መብታቸውን ያለምክንያት የሚጥስ ወይም ለማስፈራራት እና ለመቅጣት ያለመ መሆን የለበትም።

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የእስረኞች ወይም የጎብኝዎችን የውስጥ ሰውነት አካል መፈተሽ አይቻልም። ይሁን እንጂ ይህንን ለማድረግ በቂና አሳማኝ ምክንያት ሲኖር የውስጥ ሰውነት አካል ፍተሻው የሚደረገው በተከለለ ቦታ፣ በተመሳሳይ ጾታና በዘመናዊ መሣሪያ ይሆናል።

፬/ ፍተሻ የሚደረግበት ጊዜ፣ ሥርዓት፣ እና ሁኔታ እንዲሁም በፍተሻው በተገኙ የተከለከሉ ነገሮች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ይወሰናል።

፷. የጥበቃ እና ቁጥጥር ሁኔታዎች

፩/ ከማረሚያ ቤት ለማምለጥ ሲሞክር ወይም ሲዘጋጅ የተገኘ፣ በሌሎች እስረኞች ወይም በኮሚሽኑ ሠራተኞች ላይ ጉዳት ለማድረስ የሞከረ ወይም ያደረሰ፤ ወይም የማረሚያ ቤቱን ደንብና ሥርዓት ለማክበር ፍቃደኛ ያልሆነ፤ ወይም የማረሚያ ቤቱን ኃላፊዎች እና ፖሊሶች ትዕዛዝ ለመቀበል

49. Body, Property and Home Search

1/ The prison shall search visitors, property, food and drinks to be brought to prison, as well as places where prisoners work or stay only to the extent necessary to discharge its responsibilities given to it under this Proclamation related to protection of prisoners, the peace and security of the prison and the safety of the prison community.

2/ the search to be conducted in the prison shall not in any way be aimed at diminishing the dignity of the prisoners and visitors, violating their right to privacy without a reason, or to threaten or punish them.

3/ notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, it is prohibited to search the internal body parts of a prisoner. However, when there is sufficient and convincing reason to undertake such a search, it shall be done in a secluded place, by a person of same sex as the person to be searched and using modern equipment.

4/ the time, procedure and conditions on search as well as the measures to be taken on prohibited items discovered through the search shall be determined by a regulation to be issued to implement this Proclamation or relevant law.

50. Security and Inspection Conditions

1/ A prisoner who attempted or is found preparing to abscond from prison or who inflicted or attempted to inflict harm on other prisoners or employees of the Commission or is unwilling to observe the administrative regulations of the prison or refuses to accept orders from the prison officials and police

https://chilot.me

ፍቃደኛ ያልሆነ፤ ወይም በጤና ሁኔታው በራሱ ላይ ጉዳት ለማድረስ የሞከረ እስረኛ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በማረሚያ ቤቱ ግቢ ውስጥ በሚገኝ የተለየ የእስር ክፍል ውስጥ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው ቢኖርም፡-

ሀ) እስረኛን ከ፲፭ ተከታታይ ቀናት በላይ በተለየ የእስር ክፍል ውስጥ ማቆየት፤

ለ) አስረኛን በጨለማ የእስር ክፍል ውስጥ ማቆየት፤

ሐ) በተለየ የእስር ክፍል ውስጥ እንዲቆይ የተደረገን እስረኛ በቀን ውስጥ ቢያንስ ከ፫ ሰዓት ላላነሰ ጊዜ ከታሰረበት ክፍል ውስጥ ወጥቶ በክፍት ቦታ ላይ የተፈጥሮ ብርሃን እንዳያይ መከልከል፤

መ) እስረኛውን በቂ ስፋት በሌላቸው፣ የተፈጥሮ ብርሃንን ለማስገባት በማያስችሉ በቂ ስፋት ያለው መስኮት በሌላቸው፣ የጤና ሁኔታን ለአደጋ በሚያጋልጥ፣ የኤሌክትሪክ ብርሃን በሌላቸው፣ አልጋ፣ ፍራሽ እና የመኝታ አልባሳት በሌላቸው ክፍል ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ፤

ሠ) ሴቶች፣ ወጣቶች እንዲሁም በጤና ችግር ምክንያት በተለየ ክፍል ውስጥ ቢታሰሩ ለከፋ የጤና ችግር ሊዳረጉ የሚችሉ እስረኞችን በተለየ ክፍል ውስጥ እንዲታሰሩ ማድረግ፤

ረ) በተለየ የእስር ክፍል ውስጥ የታሰሩ እስረኞች የዲሲፕሊን ማጣራት ከሚወሰወደው ጊዜ በላይና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር ከሚያስገድደው ውጪ ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው እና ጠበቆቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ማድረግ ፤

የተከለከሉ ተግባራት ናቸው።

፫/ የማረሚያ ቤቱ ፖሊሶች እራሳቸውን ከጥቃት ለመከላከል ወይም በሌሎች እስረኞች ደህንነት ላይ የሚያደርስን ጉዳት ለመከላከል ወይም

officers or because of his health condition attempted to inflict harm on himself may be kept, for a limited period, in a separate prison cell within the prison.

2/ notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, the following are prohibited:

a) Keeping a prisoner in a separate cell for more than fifteen consecutive days;

b) Keeping a prisoner in a dark room;

c) Prohibiting a prisoner kept in a separate cell from going out of the room and see natural light for at least three hours a day;

d) Keeping the prisoner in a room with no sufficient space, without windows large enough to allow natural light, that endangers health, or without electric light, bed, mattress, and beddings;

e) Keeping in a separate room women or juvenile prisoners as well as prisoners who could be exposed to serious problems because of their health situation; and

f) Preventing prisoners held in separate cells from being visited by their close relatives and attorneys.

3/Prison police officers may use proportional force against those prisoners who create problems or attempt to inflict harm in accordance with the

https://chilot.me

የማረሚያ ቤቱን ደንብ እና ሥርዓት ለማስከበር ችግር በሚፈጥሩ ወይም ጉዳት ለማድረስ በሚሞክሩ እስረኞች ላይ በወንጀል ሕጉ መሠረት ተመጣጣኝ ኃይል መጠቀም ይችላሉ።

፶፩. <u>የእስር መሣሪያዎች አጠቃቀም</u>

፩/ ማረሚያ ቤት የስጋት ደረጃቸው ከፍተኛ ነው ተብሎ በተመደበው ምድብ ውስጥ የሚገኙ እስረኞች ወይም በተለየ ክፍል ውስጥ ታስረው የሚገኙ እስረኞች ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት በራሳቸው፣ በሌሎች እስረኞች ወይም በማረሚያ ቤት ፖሊሶች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ እስረኞች እንዲሁም እስረኞችን ለመጠበቅ አስፈላጊ ሲሆን ከማረሚያ ቤቱ ግቢ ውጭ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በእጅ ካቴና እንዲታሰሩ ሊያደርግ ይችላል።

1/ The prison may hand cuff prisoners who are assessed as high risk or are detained in a separate cell or who because of any reason are suspected of inflicting harm on themselves, other prisoners or prison police officers; or when the prisoners are taken out of the prison, as appropriate.

፪/ እስረኞች ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ተቋም ወይም ሕክምና ተቋም ወይም በማንኛውም መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ፊት ሲቀርቡ በካቴና አይታሰሩም።

2/ Prisoners shall not be in hand cuffs when they appear before a court or any other judicial body or a medical institution or any governmental or non-governmental institution.

፫/ እስረኞችን በካቴና የማሰር ተግባር ሰብአዊ ክብራቸውን ለማዋረድ ወይም ለማስፈራራት ያለመ መሆን የለበትም።

3/ Hand cuffs shall not be used to violate the dignity or the prisoners or to intimidate them.

፶፪. <u>የዲሲፕሊን ጥፋት እና እርምጃዎች</u>

፩/ ኮሚሽኑ እስረኛ በማረሚያ ቤት ቆይታው ስለሚፈጽማቸው ተግባሮች፣ ከሌሎች እስረኞች ወይም የማረሚያ ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ሊኖረው ስለሚገባው ግንኙነትና ፀባይ፣ ስለተከለከሉ ተግባሮች፣ ስለማረሚያ ቤቱ ደንብና ሥርዓቶች እንዲሁም የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሲፈፀሙ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ወይም ቅጣቶች ዝርዝር ሁኔታዎች የሚወስን መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ያደርጋል።

1/ The Commission shall prepare and enforce a directive that prescribes what activities a prisoner is supposed to undertake while in prison, the relations he should have with other prisoners and the prison community, the character he should have, prohibited activities, the administrative regulations of the prison, and the measures and penalties that would be imposed when a disciplinary breach is committed.

፪/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) ቢኖርም፡-

ሀ) በእስረኞች ላይ አካላዊ ድብደባ ወይም

2/ notwithstanding sub article 1 of this Article, the following are prohibited:

a) Beating or flogging of prisoners;

https://chilot.me

ግርፋት መፈፀም፤

ለ) የእስረኛውን ሰብአዊ ክብር የሚያዋርድ ተግባር መፈጸም ወይም ስድብ እና ዛቻ መሰንዘር፤

ሐ)/ እስረኛው በሚያገኘው የምግብ፣ የውሃና የህክምና አገልግሎት ላይ ገደብ መጣል፤

መ) እስረኛው ከቤተሰቦቹ ወይም ከጠበቆቹ ጋር እንዳይገናኝ ገደብ መጣል፤

ሠ) በእስረኞች ላይ የቡድን ቅጣት መፈጸም፤እና

ረ) እስረኛው ባለበት የጤና ችግር ምክንያት ለከፋ የጤና ጉዳት እንዲዳረግ የሚያስችል ቅጣት መፈፀም፤ የተከለከሉ ተግባሮች ናቸው።

b) Performing an act that degrades the prisoner or insulting or threatening him;

c) Imposing restrictions on food, water and medical services;

d) Restricting the prisoner from meeting his relatives or attorneys;

e) Inflicting group punishment on prisoners; and

f) Inflicting a punishment on a prisoner that exposes him to serious health problems because of his health conditions.

ንዑስ ክፍል አምስት
ልዩ አያያዝ የሚያስፈልጋቸው እስረኞች

SECTION FIVE
PRISONERS WHO NEED SPECIAL TREATMENT

፶፫. ሴት እስረኞች

፩/ ሴት እስረኞች የሚኖሩበት ቦታ በማረሚያ ቤት ሴት ፖሊሶች ብቻ ይጠበቃል።

፪/ ወንድ የማረሚያ ቤት ሠራተኞች ከሴት የማረሚያ ቤት ሠራተኞች ጋር በአንድነት ካልሆነ በስተቀር ሴት እስረኞች ወደሚገኙበት ቦታ መግባት አይችሉም።

፫/ ሴት እስረኞች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ወቅት ከጸታቸውና የግል ንጽህና አጠባበቃቸው ጋር በተያያዘ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁሶች ኮሚሽኑ ያቀርባል።

፬/ ሴት እስረኞች ቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው ፳፬ ወር ያላለፈው ህጻን ካላቸው አብሯቸው እንዲቆይ ይደረጋል። ኮሚሽኑ ለህጻኑ እድገትና ጤንነት አስፈላጊውን በጀት ይመድባል።

፭/ በንኡስ አንቀጽ ፶፫(፬) የተገለጸው ቢኖርም እድሜያቸው ፳፬ ወር በላይ የሆኑ ህጻናት ከታራሚ እናታቸው ጋር በማረሚያ ቤት

53. Female Prisoners

1/ The place designated for female prisoners shall only be guarded by female prison officers.

2/ Male prison workers can only enter the place where female prisoners live with female prison workers.

3/ The Commission shall supply the necessary sanitary pads for female prisoners.

4/ A child of a female prisoner who is under 24 months and who requires close attention shall stay with his mother. The Commission shall allocate the budget necessary for the growth and health of the child.

5/ Notwithstanding Sub Article 53/4/ of this provision, children's above 24 month and with court order to stay with their mothers shall provide adequate care and assistance.

https://chilot.me

እንዲቆዩ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ የማረሚያ ቤት አስተዳደሩ ለህጻኑ/ኗ እንክብካቤ እና ድጋፍ ማድረግ አለበት።

6/ Female prisoners with a child outside the prison shall be allowed to visit their child from time to time under escort or the Commission shall create the necessary condition for the meeting between the female prisoner and her child by arranging a specific place for the meeting in the prison.

፮/ ሴት እስረኞች ከማረሚያ ቤት ውጭ የሚኖር ህጻን ካላቸው በአጃቢ ፖሊስ በመውጣት ህጻኑን የሚጎበኙበትን ሁኔታ ወይም በማረሚያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ለዚሁ ዓላማ የተለየ ቦታ በማዘጋጀት እንዲገናኙ ሁኔታዎችን ኮሚሽኑ ማመቻቸት አለበት።

7/ The prison shall establish a procedure for pregnant prisoners to give birth at a hospital.

፯/ ሴት እስረኞች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የሚወልዱ ከሆነ ወደ ሆስፒታል ሄደው እንዲወልዱ የሚደረግበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል።

8/ Female prisoners shall be provided with medical follow up and care during pregnancy and after birth.

፰/ ሴት እስረኞች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በእርግዝና፣ በወሊድ እንዲሁም ከወሊድ በኋላ ተመጣጣኝ ምግብና ልዩ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል።

9/ Female prisoners shall not be forced to work during pregnancy and for one year after birth.

፱/ ሴት እስረኞች በእርግዝና እና ከወሊድ በኋላ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥራ እንዲሠሩ አይገደዱም።

፶፬. <u>ወጣት እስረኞች</u>

54. <u>Juvenile Prisoners</u>

1/ The prison shall establish a mechanism where juvenile prisoners get social, psychological, educational and recreational services.

፩/ ማረሚያ ቤት ወጣት እስረኞች የማህበራዊ፣ የሥነ-ልቦና፣ የትምህርትና የመዝናኛ አገልግሎቶችን የሚያገኙበትን አሠራር ይዘረጋል።

2/ The prison shall require juvenile prisoners to attend educational programs.

፪/ ማረሚያ ቤት ወጣት እስረኞች በትምህርት ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፉ ያስገድዳል።

3/ The prison shall arrange a separate place where juvenile prisoners can meet their parents and family.

፫/ ማረሚያ ቤት ወጣት እስረኞች ወላጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸውን የሚያገኙበት የተለየ ቦታ ያዘጋጃል።

4/ The prison shall ensure that the treatment of juvenile prisoners take into account their age.

፬/ ማረሚያ ቤቱ የወጣት እስረኞች አያያዝ ዕድሜያቸው ያገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣል።

፶፭. <u>የአካል ጉዳተኛ እስረኞች</u>

55. <u>Persons with Disability</u>

1/The Commission shall organize adequate treatment for persons with disability in full or partial impairment of

፩/ ማንኛውም እስረኛ በአፈጣጠሩ ወይም በሌላ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የአካል

https://chilot.me

ጉዳት ወይም በአዕምሮው ውስንነት ሲኖርበት ራሱን ማገዝ እንዲችል ኮሚሽኑ ተገቢውን የአያያዝ ሥርዓት ይዘረጋል።

፪/ አካል ጉዳተኞች የሚኖሩባቸው ክፍሎች፣ የመመገቢያ ክፍሎች፣ የንጽህና መጠበቂያ እና ቤተሰብ ግንኙነት ቦታዎች ምቹና ተደራሽ መደረግ አለባቸው። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2/Dormitories, dining rooms, sanitation and visitation areas shall be convenient and accessible for persons with disability. The details shall be decided by a Regulation.

፶፮. <u>ያልተፈረደባቸው እስረኞች</u>

በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ተከሳሾች እና በፍትሐ ብሔር ክርክር በማረፊያ ቤት የሚገኙ እስረኞች ከወንጀል ነጻ ሆነው የመገመት መብታቸውን ማረሚያ ቤቱ የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነት አለበት።

56. <u>Prisoners on Remand</u>

The prison shall respect the presumption of innocence of prisoners on remand and detainees of civil proceedings and ensure it is respected by others.

፶፯. <u>ሌሎች እስረኞች</u>

በጤናቸው፣ በዕድሜያቸው፣ ባለባቸው የአካል ጉዳት ወይም ሌላ ማንኛውም ምክንያት የተለየ አያያዝ ለሚያስፈልጋቸው እስረኞች ተገቢውን የአያያዝ ሥርዓት ኮሚሽኑ የመዘርጋት ኃላፊነት አለበት።

57. <u>Other Prisoners</u>

The prison shall have the responsibility to establish a system of care for the prisoners who need special treatment because of their health, age, disability or any other reason.

ክፍል ስድስት
የእስረኞች ግዴታዎች

PART SIX
OBLIGATIONS OF PRISONERS

፶፰. <u>የእስረኞች ግዴታዎች</u>

እስረኞች በዚህ አዋጅ ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተጣሉባቸው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል፡-

58. <u>Obligations of Prisoners</u>

Without prejudice to their obligations under this Proclamation as well as regulations and directives to be issued under this Proclamation, prisoners shall have the following obligations:

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት በእጀባ ወቅት በእጅ ካቴና እንዲታሰር ሲታዘዝ ተቀብሎ የመፈጸም፤

1/ Respect the order to be hand cuffed during escort as stated under sub-article (1) of Article 51 of this Proclamation;

፪/ በማረሚያ ቤቱ የፖሊስ አባሎች እና የሥራ ኃላፊዎች የሚሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ መቀበልና ትብብር የማድረግ፤

2/ Respect the lawful orders of the prison police officers and prison officials;

፫/ በማረሚያ ቤት ውስጥ የወንጀል ተግባር ሲመለከት የማሳወቅ፤ የምስክርነት ወይም የክሳሽነት ቃል የመስጠት፤

3/ Inform the prison when he is aware of a criminal activity, provide testimony or lodge complaint;

፬/ የማረሚያ ቤቱን ወደ መኖሪያ ቤት መግቢያ

4/ Respect the time for returning to cell;

https://chilot.me

የቆጠራ ሰዓት የማክበር፤

፭/ የሌሎች እስረኞች ሰብአዊ መብት እና ክብር ጠብቆ፣ ሰላምና ደህንነት አክብሮ የመኖር፤

፮/ መንግሥት እንዲገለገልበት የሚሰጠውን ማንኛውንም ንብረት በአግባቡ መጠበቅ እና ሲወጣ የማስረከብ፤

፯/ በማረም ማነፅ ባለሙያዎች የሚሰጠውን የምክር አገልግሎት በአግባቡ መቀበልና የመፈፀም፤

፰/ የሚሰጠውን ዩኒፎርም ማረሚያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መልበስ እና ፅዳቱን ጠብቆ የመጠቀም፤

፱/ ሌሎች ለማህበራዊ ግንኙነት አስፈላጊ የሆኑ ኃላፊነቶችን የመወጣት።

፶፱. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በወንጀል ሕጉና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው እስረኞችን በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አይችሉም:-

፩/ የማረሚያ ቤቱን ማህበረሰብ ሰላም እና ደህንነት በሚያውክ አድማ፣ ብጥብጥ እና ማንኛውም መሰል ተግባርን ማነሳሳት፣ መሳተፍ እና መርዳት፤

፪/ የቡድን ፀብን ማነሳሳት፣ መሳተፍ እና መርዳት፤

፫/ ሌሎች እስረኞችን ወይም የማረሚያ ቤቱ ሠራተኞችን የመሳደብ፣ የማዋረድ እና የማሸማቀቅ ተግባርን በንግግር፣ በጽሑፍ ወይም በምልክት መፈፀም፤

፬/ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወደ ማረሚያ ቤት እንዳይገቡ የተከለከሉ ነገሮችን ለማስገባት መሞከር፣ ማስገባት፣ ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም።

<u>ክፍል ሰባት</u>
<u>የቁጥጥርና የቅሬታ ሥርዓት</u>

፷.<u>ጠቅላላ</u>

5/ Respect the human rights and dignity of other prisoners and live respecting peace and security;

6/ Take proper care of the property provided to him by government for his use and hand over such property upon his release from prison;

7/ Accept and apply the advisory services provided to him by rehabilitation professionals;

8/ Wear the uniform provided to him by prison according to the directives of the prison and keep the uniform clean.

9/ Discharge other responsibilities necessary for social relations.

59. <u>Prohibited Activities</u>

Without prejudice to prohibitions under the Criminal Code and other laws the following activities are prohibited in the prison:

1/ Instigate, participate or assist a conspiracy, disturbance or similar activities that disturb the peace and security of the prison community;

2/ Instigate participate or assist group brawl;

3/ Engage in, orally, in writing or through signs, insulting, degrading and intimidating activities against other prisoners or prison employees;

4/ Use, possess, bring into prison or attempt to bring into prison things that are prohibited by a directive issued by the Commission.

<u>PART SEVEN</u>
<u>CONTROL AND COMPLAINT PROCEDURE</u>

60. <u>General</u>

The prison, in order to protect the dignity and

https://chilot.me

ማረሚያ ቤቱ የእስረኞች ሰብዓዊ ክብርና መሠረታዊ መብቶች ለማስከበር፣ በማረሚያ ቤት ውስጥ ማንኛውንም ጥቃት፣ ማሰቃየት፣ ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ሰብአዊነት የጎደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረትና ለመከላከል፣ እንዲሁም የማረሚያ ቤቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ፤

፩/ የውስጥና የውጭ ቁጥጥር በመዘርጋት ተግባራዊ ያደረጋል፤

፪/ እንደሁኔታው በሦስተኛ ወገን መጎብኘት ይፈቀዳል፤

፫/ የእስረኞች ቅሬታ የማቅረብ መብት ያከብራል።

፷፩. <u>የውስጥ ቁጥጥር</u>

፩/በማረሚያ ቤቱ የሚዘረጋ ቋሚ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ይኖራል። ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፪/ የማረሚያ ቤት ቋሚ ቁጥጥር እንዳለ ሆኖ ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ ተቆጣጣሪዎች በመላክ እንደአስፈላጊነቱ በቋሚነት ሊቆጣጠር ይችላል።

፫/ በማህበረሰብ መሪዎች ቦርድ ተከታታይነት ያለው ቁጥጥር ይደረጋል።

፷፪. <u>የውጭ ቁጥጥር</u>

፩/ በሌላ ሕግ የተሰጣቸው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የሚመለከታቸው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና አባላት፣ የእንባ ጠባቂ ተቋም፣ ዓቃቢ ሕግ፣ እንዲሁም በሕግ የማረሚያ ቤትን የመቆጣጠርና የመጎብኘት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት በማንኛውም ጊዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ማረሚያ ቤቶችን የመጎብኘት፣ ቅሬታ ያላቸውን እስረኞች የማነጋገር፣ የእስረኞችን መዝገብ የመመርመር፣ የማረሚያ ቤት ሠራተኞችን፣ ፖሊሶችን እንዲሁም ኃላፊዎችን የማናገርና ውጤቱን ከማሻሻያ ሃሳብና እርምጃ ጋር ለሚመለከታቸው

fundamental rights of prisoners, to abolish any attack, torture or any other cruel, inhuman and degrading treatments and punishments as well as to realize its objectives shall:

1/ Establish and implement Internal and external control;

2/ Permit third party visit as appropriate; and

3/ Respect the right of prisoners to lodge a complaint.

61. <u>Internal Control</u>

1/ There shall be an internal control system to be developed by the prison. Particulars shall be determined by a directive;

2/ In addition to the prison permanent control, the Attorney General may, as appropriate, perform regular control on prisons.

3/ There shall be continuous supervision by the Board of Community Leaders.

62.<u>External Control</u>

1/ Without prejudice to powers given to them under other law, the Ethiopian Human Rights Commission, relevant Standing Committees and members of the House of Peoples Representatives, the Office of the Ombudsperson, as well as other bodies empowered by law to inspect and visit prisons shall have without prior notice the power to visit prisons, speak to prisoners with complaints, examine prisoner registry as well as discuss with prison employees, police officers, prison officials and communicate their findings with recommendations to the concerned government bodies and to the public.

https://chilot.me

የመንግሥት አካላትናለሕዝብ የማሳወቅ ሥልጣን አላቸው።

፪/ እስረኞች መብቶች ለማስከበርና የአያያዝ ሁኔታቸውን ለማሻሻል በማሰብ የተቋቋሙ የሲቪል ማህበራት፣ የምርምር ተቋማት ወይም ተመራማሪዎች በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን የቁጥጥር ተግባራት አስቀድመው ለማረሚያ ቤቱ በማስፈቀድ ማከናወን ይችላሉ።

፫/ ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ወይም ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተቋቋሙ ኮሚሽኖች፣ ኮሚቴዎች፣ ራፖርተሮችና የመሳሰሉት በጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ ሲፈቀድ በንዑስ አንቀፅ (፩) የተቀመጠውን የመጎብኘትና የመመርመር እንዲሁም ሪፖርት የማቅረብ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ።

፷፫. <u>የመገናኛ ብዙሃን ግንኙነት</u>

፩/ ኮሚሽኑ የእስረኞችን አያያዝ ለማሻሻል እና ዜጎች መረጃ የማግኘት መብታቸውን ማረጋገጥ እንዲችሉ የመገናኛ ብዙሃን ስለእስረኞች አያያዝ ጉብኝት ማድረግ ይችላሉ።"

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለማረምና ለማነጽ ስጋት የሆነ የፀጥታ ችግር መኖሩ ሲረጋገጥ ኮሚሽኑ የመገናኛ ብዙሃንን ጉብኝት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲቋረጥ ሊያደርግ ይችላል።

፷፬. <u>ቅሬታ ስለማቅረብ</u>

፩/ እስረኛ አያያዙን፣ የዲሲፕሊን አቤቱታ እና የተሰጠበትን ውሳኔ አስመልክቶ ቅሬታ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው።

፪/ ቅሬታውን እስረኛው፣ በዘመዶቹ፣ በሕግ አማካሪው ወይም ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ ሌሎች ሰዎች ሊያቀርቡ ይችላሉ።

፫/ የቅሬታ አቀራረብ ምሥጢራዊነት ይጠበቃል።

፬/ ቅሬታ በመቅረቡ ምክንያት ብቀላ፣ ማስፈራራትና ሌሎች አሉታዊ ተግባራትን መፈፀም የተከለከለ ነው።

2/ Civic organizations established to protect the rights of prisoners and promote their better treatment, research institutions or researchers have the right to undertake the activities under sub-article (1) of this Article having secured prior permission from the prison.

3/ Commissions, Committees, Rapporteurs and similar bodies established under a treaty to which Ethiopia is a member may undertake the visiting, inspecting and reporting provided for under sub-article (1) of this article upon the permission of the Attorney General.

63. <u>Broadcast Visitation</u>

1/ to enhance treatment of prisoners and realize access to information for citizens broadcasters may visit prison facilities.

2/ Withstanding sub article 1 of this provisions, the Commission may terminate the visitation in whole or part where advert threat occur to rehabilitation discourse.

64. <u>Lodging a Complaint</u>

1/ A prisoner shall have the right to lodge a complaint about his treatment, a disciplinary action instituted and penalty imposed on him.

2/ The complaint may be lodged by the prisoner, his relatives, his attorney or any other interested person.

3/ The complaint shall be kept confidential.

4/ Retaliating, intimidating or performing any other similar actions on a prisoner because of the compliant is prohibited.

https://chilot.me

፫/ የቅሬታ አቀራረቡ ዝርዝር ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፷፭.የፍርድ ቤት ሥልጣን

፩/ እስረኛው በዚህ ክፍል ላቀረባቸው ቅሬታዎች መልስ ካላገኘ ወይም ውድቅ ከተደረገበት ቅሬታውን ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለት ወር ጊዜ ሊያቀርብ ይችላል።

፪/ ፍርድ ቤቱ ክርክሩንና የማረሚያ ቤት ኃላፊዎችን እንደነገሩ ሁኔታ ከሰማ በኋላ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተገቢ ነው ብሎ የሚያምነውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይሰጣል።

ክፍል ስምንት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፷፮. በማረሚያ ቤቶች ለእስረኞች የሚሰጡ ልዩ ጥቅሞች

፩/ ማረሚያ ቤቶች በዚህ አዋጅ የተደነገገውን የማረም፣ የማነፅና መልሶ ወደ ሕብረተሰቡ የመቀላቀል ዓላማቸውን ለማሳካት በሚያደርጉት የማረም ጥረት በመልካም ሥነ ምግባር ለሚመሩ፣ ለሕብረተሰቡ አደገኝነት ለሌላቸውና አርአያ ለሆኑ እስረኞች እንደነገሩ ሁኔታ የማበረታቻ ጥቅም ሊሰጧቸው ይችላሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማረሚያ ቤት ለእስረኛው፡-

ሀ) ከፍተኛ ጥበቃ ካለው ማረሚያ ቤት ወደ ዝቅተኛ ጥበቃ ያለው ማዘዋወር፤

ለ) ከማረሚያ ቤት ውጭ ሄዶ የመሥራት እና ለሠራውም ሥራ የተሻለ ክፍያ መክፈል፤

ሐ) የፍርድ ጊዜያቸውን በማጠናቀቅ ላይ ያሉ በመልካም ሥነ-ምግባራቸው የሚታወቁ እና ከእስር ቤት የማምለጥ ስጋት የላቸውም ብሎ የለያቸውን እስረኞች ያለ አጃቢ ፖሊስ ወጥተው ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተገናኝተው

5/ Particulars on lodging of complaints shall be determined by a directive to be issued by the Commission.

65. Power of the Court

1/A prisoner whose complaints under this section has not been addressed or has been rejected may lodge his complaints to the First Instance Court within two months.

2/The court, after having heard the complaints and the prions officials as appropriate, make a decision or order it considers appropriate based on this Proclamation and other relevant laws.

PART EIGHT
MISCELLANEOUS PROVISIONS

66. Special Benefits to Prisoners

1/ With a view to achieving their objective of rehabilitation and re-integration in to society of prisoners as provided in this Proclamation and depending on circumstances, prisons may provide special benefits to prisoners with good conduct who are not taught to be dangerous to society.

2/ Without prejudice to sub-article (1)of this Article prisons may:

a) ransfer a prisoner from maximum security prison to ordinary prison facility.

b) allow the prisoner to work outside of the prison and get a better payment for his work

c) permit prisoners with good conduct who are completing their sentence and have no risk of escape to visit their families and return to prison without police escort.

https://chilot.me

የሚመለሱበትን ሁኔታ መፍቀድ፤

መ) ሌሎች ኮሚሽኑ እስረኞችን በሥነ ምግባር ያንፃል፣ ያርማል ወይም ፍርድን ሲጨርስ ወደ ህብረተሰቡ በተሟላ ሁኔታ ለመቀላቀል ይረዳል ወይም ያስችላል ያለውን ልዩ ማበረታቻ መስጠት ፤

ይችላል።

፷፮. <u>አመክሮና ከእስር ስለመለቀቅ</u>

፩/ በወንጀል ሕጉና ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለአመክሮ የሚያበቁ መመዘኛዎችን ላሟላ እስረኛ ማረሚያ ቤቱ ፍርዱን ከሰጠው ፍርድ ቤት አመክሮ ይጠይቅለታል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

፪/ እስረኞች ከእስር ሲለቀቁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ መሠረት ማረሚያ ቤቱ የተረከባቸውን ገንዘብና ንብረቶች መልሶ የማስረከብ ግዴታ አለበት።

፷፯.<u>ከክልል ማረሚያ ቤት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት</u>

፩/ የኮሚሽኑና የክልል ማረሚያ ቤቶች በሕግ የተሰጣቸው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል የጋራ ጉባኤ ያቋቁማሉ።

፪/ የጋራ ጉባኤው የሚመራበት የራሱ ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፫/ የጋራ ጉባዔው አባላት በሚከተሉት ዓላማዎች በመደጋገፍና በትብብር ለመሥራት የሚያስችል ይሆናል፡-

ሀ) በመንግሥት የሚወጡ ሀገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችን እና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ ይሠራሉ፤

ለ) የጥበቃ፣ የደህንነት፣ የመሠረታዊ ፍላጎት፣ የማረም እና ማነፅ ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

ሐ) ሐገራዊ የማረሚያ ቤቶችን አገልግሎት ለማሻሻል ተቀራራቢነት ያለው እንዲሆን የሚያስችል ጥናትና ምርምር በማድረግ፣

d) In accordance with a directive to be issued by the Commission, provide other special privileges to prisoners which may help them to rehabilitate and fully reintegrate with the community after serving their sentence.

67. <u>Parole and Release</u>

1/ Where conditions are fulfilled, the prison administration shall in accordance with the Criminal Code and directive to be issued by the Commission request parole for prisoners.

2/ The prison has the responsibility to return money and other belongings of prisoners in accordance Article 31 of this Proclamation.

68. <u>Relationship with Regional Prisons</u>

1/ Without prejudice to the respective legal mandate provided by law, the Commission and Regional prisons shall establish a joint council to enable them strengthens their working relationship.

2/ The joint council shall have its own internal rules and procedure.

3/ The joint council shall cooperate on:

a) national polices and strategies of issued by the government and on current issues,

b) Prepare and follow up implement of standards on security, custody, basic provisions and rehabilitation of prisoners.

c) Improving national correctional service, researching best practices and expand implementation of such good practices.

https://chilot.me

ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

መ) በማረሚያ ፖሊስ ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ቅጥርና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ ይሠራሉ፤

ሠ) የእስረኞች የመረጃና ስታትስቲክስ ልውውጥ ሥርዓት ይዘረጋሉ፤

ረ) በማረሚያ ፖሊስ ምልመላና ቅጥር፣ በትምህርትና ስልጠና፣ በማዕረግ አሰጣጥ፣ በደንብ ልብስ አለባበስ፣ በትጥቅና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ሀገር አቀፍ ስታንዳርድ ያወጣል።

፷፱. <u>የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት</u>

ከኮሚሽኑ ተልዕኮ ጋር በተያያዘ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች በወንጀል ሕጉ ለፖሊስ አባል የተደነገገው ለማረሚያ ፖሊስ አባልም ተፈጻሚ ይሆናል።

፸. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፪፻፫ (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፸፩. <u>መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፪፻፫ ለፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ተሰጥተዉ የነበሩ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሰረት እንደገና ለተቋቋመዉ ለፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፸፪. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ

d) Work jointly on the selection, training and recruitment, and other administrative matters.

e) Establish system for prisoner's statistics and data exchange.

f) Establish national standard for the selection, training, ranking, uniform, armament of prison police and other related matters.

69. <u>Application of Provisions of the Criminal Code</u>

Provisions of the Criminal Code applicable for the police shall mutatis mutandis also apply for prison police on crimes committed in connection with the mission of the Commission.

70. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ Federal Prison Commission Establishment Proclamations No.365/2003 (as amended) is hereby repealed by this Proclamation.

2/ Any law, regulation, directive or practice inconsistent with this Proclamation shall not be applicable on matters covered under this Proclamation.

71. <u>Transfer of Rights and Responsibilities</u>

Rights and responsibilities conferred to Federal Prison Commission under Proclamation No.365/2003 are hereby transferred to Federal Prison Commission re-established by this Proclamation.

72. <u>Power to Issue Regulations</u>

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this

https://chilot.me

ይችላል።

፪/ ኮሚሽኑ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፷፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Proclamation.

2/ The Commission may issue Directives necessary for the implementation of the regulations that may be issued in accordance with sub-article (1) of this Article.

73. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come in to force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

Done at Addis Ababa, this 17th day of February,2020

SAHELEWORK ZEWEDE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF ETHIOPIA